



# የእይታና የትወና ጥበባት




## 2ኛ ክፍል

## የተማሪ መጽሐፍ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 2ኛ ክፍል


**አስማምቶ አዘጋጆች፡-**

አምዶም ገ/ዮሃንስ ጉማይዴ ጉልአ

ርብቃ ፀጋዬ ታምራት አብርሀም

**አርትኦት፡-** ምንያህል በቀለ

**ሰዓሊ፡-** አምዶም ገ/ዮሃንስ

**ኖታ ቀራጭ፡-** ርብቃ ፀጋ

**የጥራት ተቆጣጣሪ**

ተክለማርያም ጥላሁን ተዋበ ታደሰ

**አጽዳቂዎች(ቫሊዴተር)**

ተስፈዬ እሸቱ ዋንቱሳ ጉንሳ

ሲዳሞ ሳለሰ ይመኙሻል ዩሱፍ

ቅድስት ደፋር ሀብታሙ ጳውሎ

**ሌያውት ዲዛይን፡-** ኃይለማርያም መለሰ



የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# © የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቶ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል።

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው።

# ማውጫ

መግቢያ ........................................................................................ i

## ምዕራፍ 1 .................................1

### መለየት ...................................................... 1

1.1. የሙዚቃ ኖታዎችን እና እረፍቶችን መለየት ............................ 1

1.2. ቀለል ያሉ እንቅስቃሴዎች እና ውዝዋዜዎችን መለየት ............... 4

1.3. ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታዎችን ማየት ...................................... 5

1.4. ፎቶዎችን መመልከት ............................................................. 7

1.5. የእለት ተእለት ማህበረሰባዊ ክንዋኔዎች .................................. 22

## ምዕራፍ 2 .................................27

### ፈጠራዊ አገላለፅ .......................................... 27

2.1. የሙዚቃ ኖታዎችን መጫወት ............................................ 28

2.2. ቀለል ያሉ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ....................................... 31

2.3. ቀላል የትወና ጨዋታዎችን መጫወት ..................................... 32

2.4. ቀለል ያሉ መስመሮች በመጠቀም መቸክቸክ እና የመስመር ንድፎችን መለማመድ ............................................................ 33

## ምዕራፍ 3 .................................44

### ሀገረ-ሰባዊ ምልከታዎች .............................. 44

3.1. ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ........................................ 45

3.2. ተዛማጅ ታሪኮች ............................................................ 51

3.3. ትወና ከባህላዊ ምልከታ አኳያ .............................................. 59

## ምዕራፍ 4 .............................62
### አድናቂነት ........................................... 62
4.1. የእይታ እና የትወና ጥበብ ክንዋኔዎች ........................................ 63

## ምዕራፍ 5 .............................72
### ግንኙነት ................................................. 72
5.1. ሙዚቃ እና የእይታ ጥበባት ግንኙነት ........................................ 73
5.2. በሰውነት አካላት የሚሰሩ ሙዚቃዎች ........................................ 75
5.3. የእይታ እና የትወና ጥበባት ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ለማገዝ ያለው ጠቀሜታ ........................................ 77

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የትውን እና የእይታ ጥበባት ለሁለተኛ ክፍል ሲሆን በአከባቢያችን ከሚገኙ ተፈጥሮኣዊ እና ሰዉ ሰራሽ ቁሶች የሚቆራኙ እሴቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ትውኔት ፤የእይታ ጥበብ እና የሙዚቃ ኖታዎችን በመጠቀም መስመሮች እና የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን በመጠቀም የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች የትውን እና የእይታ ጥበባትን ተጠቅማቹ በእየለቱ የምታስተውሏቸው ነገሮች መነሻ በማድረግ የትውን እና የእይታ ጥበባትን መለየትና ለፈጠራ ያላችሁን ልምድ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ የክፍል ደረጃ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታዎችን ታውቃላችሁ
- ቀለል ያሉ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ትለያላችሁ
- ፎቶዎች እና ምስሎችን ለይታችሁ ታውቃላችሁ
- መስመሮች በመጠቀም ንድፎችን ትለማመዳላቹ
- ሙዚቃ፣ውዝዋዜ እና ተውኔት በመጠቀም ተዛማጅ ታሪኮችን ትከውናላችሁ
- በከባቢያችሁ ላይ ያሉ ቀለማትን ትለያላችሁ
- የትወና እና የእይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ያለው ግንኙነት ትገልፃላችሁ

# እንማር



እንማር እንማር
እንመራመር
ትምህርት ያስፈልጋል
በዕውቀት ለመኖር
ተፈጥሮን ህይወትን
ለመቃኘት በውል
ድራማ ሙዚቃ
ደግሞ ስነ-ስዕል
ማስተማርያ ናቸው
እያዝናኑ እኛን
አበባ እና አበበ
እስኪ ይንገሩን




**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡**

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የሙዚቃ ኖታዎችን እና ቀላል እንቅስቃሴ ትለያላችሁ
- ልጆች ግማሽ የኖታ መጠን ያላቸው ሙዚቃዎች ትለያላችሁ
- ፎቶ ወይም ምስል በመመልከት ሀሳቡን ትረዳላችሁ
- ፎቶ ወይም ምስል በመመልከት አከባቢያችሁን እና ሃገራችሁን ታውቃላችሁ

## 1.1.የሙዚቃ ኖታዎችን እና እረፍቶችን መለየት

### መግቢያ

በሙዚቃ ውስጥ የተለያዩ ኖታዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥ በዚህ ክፍል የምንመለከተው ሁለቱን ይሆናል።

## ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ

- የሙዚቃ ኖታዎችን እና የዕረፍት ኖታዎችን ከሙሉ እስከ ግማሽ ትለያላችሁ
- የሙዚቃ ኖታዎችን ሙሉና ግማሽ እንዲሁም የጊዜ ዋጋን ታውቃላችሁ
- ሙሉ እና ግማሽ ኖታዎችን እና የዕረፍት ኖታዎችን ቅርፅ ትለያላችሁ
- የተለያዩ ሙዚቃዊ እንቅስቃሴዎችን እና ውዝዋዜን ታውቃላችሁ

### ሙሉ የሙዚቃ ኖታ፡- ከሙሉ ዕረፍት ጋር እና ግማሽ የሙዚቃ ኖታ ከግማሽ ዕረፍት ጋር

በመጀመሪያ ኖታ የምንለው የሙዚቃ ፊደላትን ነዉ፡፡ ሙሉ የሙዚቃ ኖታ በውስጡ 4 ምት ያለው ሲሆን በጊዜ ዋጋ ከሁለት ግማሽ ኖታዎች ጋር እኩል ነው፡፡

ለምሳሌ፡- አራት የቆይታ ጊዜ ያለውን ኖታ ሁለት ቦታ በመክፈል ከሁለት ግማሽ ኖታ ጋር እኩል እንደሆነ እናያለን፡፡




**ሙሉ የሙዚቃ እረፍት፡-** ማለት በውስጡ አራት የጸጥታ (የእረፍት) ጊዜ አለው፡፡ ሙሉ የሙዚቃ እረፍት ኖታ በጊዜ ዋጋ ከሁለት ግማሽ እረፍት ኖታ ጋር እኩል ነው፡

 ወይም 

ግማሽ የሙዚቃ ኖታ:- ግማሽ የሙዚቃ ኖታ ማለት ሁለተኛው የኖታ ዓይነት ሲሆን በውስጡ ሁለት ምት አለው::

ግማሽ የዕረፍት ኖታ ሁለት ምት በዝምታአለዉ ።



የሙዚቃ ኖታዎች ስም ያላቸው የጊዜ ቆይታ እና የዕረፍት ምልክት

| የሙዚቃ ኖታዎች ስም | ያላቸው የጊዜ ቆይታ | የዕርፍት ምልክት |
|---|---|---|
| O ሙሉ ኖታ | 4 ምት |  |
| h ግማሽ ኖታ | 2 ምት |  |

ሰንጠረዥ 1.1፡ የሙዚቃ ኖታዎች ስም እና ምልክቶች

## መልመጃ 1.1

ከዚህ በታች ያሉትን(የተዘረዘሩትን) ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱን አስቀምጡ

1. በሙዚቃ ውስጥ የመነሻ ኖታ የምንለው ሙሉ ኖታ እና ሙሉ ዕረፍት ምልክትን ነው::
2. ሙሉ የሙዚቃ ኖታ በውስጡ አራት ምት በድምፅ አለው::
3. ሙሉ የዕረፍት ምልክት በውስጡ አራት ምት በዝምታ አለው::
4. ግማሽ የሙዚቃ ኖታ በውስጡ ሁለት ምት በድምፅ አለው

## 1.2. ቀለል ያሉ እንቅስቃሴዎች እና ውዝዋዜዎችን መለየት

### መግቢያ

እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ተዛማጅነት ያላቸው የአካል እንቅስቃሴ ናቸው፡፡ እንቅስቃሴ በቦታ መካከል ባሉ ነጥቦች መሀከል አካላዊ እንቅስቃሴ ሲሆን ውዝዋዜ ደግሞ ለሙዚቃ በሚመታ ስልተምት (ሪቲም) በእርምጃ እግሮቻችንን፤ አካላችንን በተራቀቀ መንገድ ማወዛወዝ፤ማንቀሳቀስ እና በመሳሰሉት መንገዶች የሚተገበር ክንዋኔ ነው፡፡

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ቀለል ያሉ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ታያላችሁ
- ስልተ ምትን (ሪትም) ጠብቃችሁ መንቀሳቀስ ታውቃላችሁ

### ማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች በሙዚቃ ዉስጥ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡

### ደስተኛ የሆነ

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ ቸብቸብ 2×
ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ ቸብቸብ
ደስተኛ የሆነ ይደንስ ዳንስ ዳንስ 2×
ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ ይደንስ ዳንስ ዳንስ
ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ ሀ ሀ ሀ ሀ 2×
ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ ሀ ሀ ሀ ሀ

ደስተኛ የሆነ ወደ ላይ ይዝለል ዘለል ዘለል
ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ ወደ ላይ ይዝለል ዘለል ዘለል



ምስል 1.1፡ ደስተኛ የሆነ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ

### መልመጃ 1.2

- ይህን የተግባር መልመጃ በክፍል ላሉ ተማሪዎች እና ለመምህሩ በማሳየት ይመልሱ፡፡

1. ደስተኛ የሆነ የሚለውን መዝሙር በአከባቢያቹ ዜማ በእንቅስቃሴ እና በውዝዋዜ አሳዩ፡፡
2. በቡድን በቡድን በመሆን ቀድሞ የሚታውቁትን መዝሙሮች ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘምሩ፡፡

## 1.3. ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታዎችን ማየት

### መግቢያ

ቀለል ያሉ እንቅስቃሴዎችንና ውዝዋዜን ህጻናት እያደረጉ የራሳቸውን

አዕምሮ የሚያድሱበት ዘዴ ነው። የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ከውዝዋዜዎች ጋር እያዛመዱ የሚተገበሩበት መንገድ ነው።

## ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ

- ቀለል ያሉ የጨዋታ ዓይነቶች ታውቃላችሁ
- ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታ ታያላችሁ ማነቃቂያ ጥያቄ
- የጨዋታ ዓይነቶች ዘርዝሩ?
- ትወና ምን ማለት ነው?

**ቀለል ያለ የትወና ጨዋታ፡-** የምንለው ትወናን የሰው ልጆች በህፃንነታቸው በየአከባቢያቸው የሚጫወቱት ዕቃ ዕቃ ብለው የተለያዩ ቁሶችን በመሰብሰብ ቤት መሰል ነገር አበጅተው በቤት ውስጥ የሚገኘውን ቁሶችን በተለያዩ የወደቁ ዕቃዎችን በመሰብሰብ አበጃጅተው እናት፣አባት፣ልጅ ተባብለው ገፀ-ባህሪያት በመክፈል አባት የአባትን ድርጊቶች እናትም ልጅም በቤት ውስጥ ያዩትን የሚያስሉበት ጨዋታ ነው።

**ለምሳሌ** አባት ሥራ ሄዶ ሲመጣ እናት የሚበላ ታቀርባለች ልጅ እጅ ያስታጥባል መሰል ተግባሮችን በቤታቸው ያዩትን ያስመስላሉ ይህ ደግሞ ቀላል የትወና ጨዋታ ሲሆን ሰዎች መተወንን ከዚሁ ይጀምራሉ። ራሳቸውን እያወቁ እያደጉ ሲመጡ ድርጊቶቻቸውም እያደገ ይመጣል ፈጠራንም በመጠቀም የተለያዩ ድርጊቶችንም እየጨመሩ ያመጣሉ።

ለምሳሌ የልጅ ገፀ- ባህሪ የምጫወተው እንድያለቅስ በማድረግ እናት ስታባብል አባት ከረሜላ ብስኩት እገዛልሃለው ብሎ ወደ ሥራ ሄዶ ሲመለስ ቁሶችን ይዞ ይመጣል ልጅም እንደ ብስኩት እንደ ከሬሜላ በማስመሰል ከበሉ በኋላ የምደሰቱትን የደስታ ስሜት ያንፀባርቃሉ ይህ ልጆች ጨዋታ ለትወና መሠረት ነው።

### መልመጃ 1.3

1. የዕቃዕቃ ጨዋታ በመጫወት ለመምህራችሁ አሳዩ



ምስል 1.2፡ ቀለል ያለ የትወና ጨዋታ

## 1.4. ፎቶዎችን መመልከት

### መግቢያ

ተማሪዎች፡- በዚህ ርዕስ የተለያዩ ክንዋኔ እና ሀሳብ ያላቸው ምስሎች(ፎቶገራፍ) በማየት የምን ምስል እንደሆነና ምስሉ ላይ ምን እየተከናወነ እንደሆነ በመለየት አከባቢያችሁን እንድትረዱ እና ዝንባሌን እንድታዳብሩ እና ሀሳብ የመግለፅ ችሎታችሁን ለማዳበር ይረዳል::

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ

- የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች እና ቅርሶች ምስል ታውቃላችሁ
- የዕደ-ጥበብ ውጤቶች በማወቅ ታደንቃላችሁ
- የቤት እንስሳት እና የዱር እንስሳት ለይታችሁ በማወቅ ታደንቃላችሁ
- የማጓጓዣ አይነቶችን ትመለከታላችሁ
- ባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያዎችን ትመለከታላችሁ
- የብርሃን ምንጮች ለይታችሁ ታውቃላችሁ

## ሀ. የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች


**ተማሪዎች፡-** ኢትዮጵያ ሀገራችን ብዙ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች አሉዋት፡፡ ከነዚህ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች ለመጎብኘት ብዙ የውጭ ዜጎች ስለሚመጡ እንደ ገቢ ምነጭ ሆኖው ያገለግላሉ፡፡

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- የተፈጥሮ መስህብ ምን ማለት ነው?
- ተማሪዎች እስቲ አከባቢያችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች ለአስተማሪያችሁ ዘርዝሩ?




ምስል 1.3፡ የእግዜር ድልድይ በአበያ እና ጫሞ መሀል የሚገኝ ተራራ



ምስል 1.4፡ በጋሞ ዞን የሚገኝ ነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ



ምስል 1.5፡ በኮንታ እና በዳውሮ መሀል የሚገኝ ጨበራ-ጩርጩራ ብሄራዊ ፓርክ



ምስል 1.6፡ በደቡብ ኦሞ ዞን የሚገኝ ማጎ ብሄራዊ ፓርክ

## ለ. ቅርሶች

- ዋካ (ከ እንጨት የሚሰራ ቅርፅ)

ዋካ በኮንሶ የሚገኝ ከእንጨት የሚሰራ ቅርፅ ሲሆን በ ዓለም አቀፍ የቅርሳቅርስ መዝገብ ከሰፈሩት የኢትዮጵያ ቅርሶች አንዱ ነው።



ምስል 1.4፡ ዋካ በኮንሶ የሚገኝ ከእንጨት የሚሰራ ቅርፅ ጥያ ትክል ድንጋይ

ጥያ ትክል ድንጋይ በጉራጌ ዞን የሚገኝ ድንጋይ ላይ የተሰሩ ቅርፆች ናቸው፡፡



ምስል 1.4፡ ጥያ ትክል ድንጋይ አክሱም ትክል ድንጋይ

አክሱም ትክል ድንጋይ በትግራይ ክልል የሚገኝ ከአንድ ወጥ ድንጋይ የተሰራ ሲሆን በዓለም አቀፍ ቅርስነት ከተመዘገቡት የኢትዮጵያ ቅርሳቅርሶች አንዱ ናው፡፡




ምስል 1.9፡ አክሱም ትክል ድንጋይ

## ሐ. የዕደ-ጥበብ ውጤቶች

- የተለያዩ የቤት አሰራሮች

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ቤት ከምን ከምን ይሰራል?
- በአከባቢያችሁ የሚገኙ የቤት አሰራር ዓይነቶችን ዘርዝሩ?



ምስል 1.10፡ ባህላዊ የቤት አሰራር

- መጀመሪያ የመስርያ ቦታ ማዘጋጀትና በሜትር ለክቶ ቦታውን ማስተካከል
- የመስሪያ ቀርከሃ እና የተለያዩ እንጨቶች ማሰባሰብ
- ለምሶሶ የሚያገለግል ከፅድ፣ከባህርዛፍ ወይም ኮሶ እንጨት ማዘጋጀት::
- የግድግዳ እንጨቶችን ማቆምና በግድግዳ ላይ ማገሮችን መምታት::
- (ማሴሪ) ከዚያ መሶሶ ማቆሚያ ቦታ መቆፈርና መሶሶ እንጨቱን ማቆም::
- በምሶሶ ላይ ጣሪያ መምታት በጣሪያ ወይም ማገሮችን ወይም የተዘጋጁ ቀርከሃዎች በገመድ ወይም በወፊቾ ማሰር::
- የቤቱ መግቢያ በር ማዘጋጀት::
- ለቤቱ ክዳን የሚያገለግሉ ሰንበሌጥ ወይም የስንዴ፣የገብስ የደረቀ ሳር ማሰባሰብና ቤቱን ዝናብ እንዳይገባ አድርጎ መክደን::
- በውስጡ የመኝታ ክፍል እና የዕቃ ማስቀመጫ ክፍሎችን መሥራት (የዕቃ ማስቀመጫ መደርደሪያዎችን በመሥራት በደንብ አድርጎ በጭቃ መለሰን::



ምስል 1.11፡ የተለያዩ የቤት አሰራሮች

## መልመጃ 1.4

2. ቤት ከምን ከምን ይሰራል?
3. ዋካ(ኮንሶ)ከምን የተሰራ ቅረፅ ነው?
4. ጨበራጩርጩራ ብሄራዊ ፓርክ የት የገኛል?
5. የተፈጥሮ መስህብ ምን ማለት ነው?


- የሽመና ስራዎች

## የማነቃቂያ ጥያቄ

- አልባሳት ከምን ይዘጋጃሉ?
- ሽመና ምንድን ነው?
- በአከባቢያቹ የሚገኙ የሽማ ውጤቶችን ዘርዝሩ?

የሽማ ሥራ ከተለያዩ ክር (ማግ) የሚስራ የሥራ አካል ነው በአከባቢያችን የሚገኙ የጥበብ ልብሶች ከሽማ ሥራ የተገኙ ናቸው፡፡

**ለምሳሌ**፡-የተለያዩjአልባሳቶች፣ሽሚዝ፣ጃፖኒ፣ሱሪ፣ቀሚስ፣ካናቲራ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡




ምስል 1.12፡ የተለያዩ አልባሳቶች

## የሸክላ ስራዎች

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ከ አፈር የሚሰሩ የቤት ቁሳቁሶች ዘርዝሩ?
- ጀበና ለምን ኣገልግሎት ይውላል?

የሸክላ ሥራ ከተለያዩ ከአፈር ዓይነቶች ይሰራሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-** ከጥቁር አፈር፣ከቀይ አፈር ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

የሸክላ ሥራ ውጤቶች የሚባሉ ጀበና፣እንስራ፣ገንቦ፣ዋንጫ፣ እንክሪት(ማንደጃ) ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡


እንስራ


ጀበና


እንክሪት


ድስት

ምስል 1.13፡ የሸክላ ስራዎች

## የእንጨት ውጤቶች

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- እንጨት ከምን የገኛል?
- በአከባቢያችሁ የሚገኙ የእንጨት ውጤቶችን ዘርዝሩ?

የእንጨት ውጤቶች ከተለያዩ እፅዋቶች ይዘጋጃሉ፡፡


የእንጨት ውጤቶች የምባሉት በርጩማ፣ጠሬጴዛ፣ወንበር እና ቁምሳጥን በብዛት የምንገለገልባቸው የእንጨት ውጤቶች ናቸው፡፡ እነዚህን ውጤቶች ለመቀመጫነት፣ለምግብ ማቅረብያ እና ለመፃፊያነትም እንጠቀምባቸዋለን፡፡



ቦርኮታ



በርጩማ



ወንበር




ጠረጴዛ

ምስል 1.14፡ የእንጨት ውጤቶች

## ሠ. የቤት እና የዱር እንስሳት

### የቤት እንስሳት

የቤት እንስሳት ከሰው ልጅ ተላምደው ቤት ውስጥ የሚኖሩ እና የተለያዩ አገልግሎት እና ጥቅም የሚሰጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡ -ፈረስ፣ላም፣ደሮ፣በግ፣ፍየል፣አህያ፣ድመት፣ውሻ ወ.ዘ.ተ.ናቸው፡፡





ምስል 1.15፡ የቤት እንስሳት

## የዱር እንስሳት

የዱር እንስሳት ማለት ዱር ውሰጥ ወይም በመካነ-እንስሳት የሚኖሩ እንስሳት ሲሆኑ፤የቱሪስት መስህብ በመሆን ለአገራችን የገቢ ምንጭ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

**ለምሳሌ፡**ዝሆን፤ቀጭኔ፣ነብር፣ከርከሮ፣ጉማሬ፣ዜብራ፣አዞ፣ጅብ፣ቆርኪ፣ጎሽ፣ጦጣ፣የተለያዩ አዕዋፋት ወ.ዘ.ተ.ናቸው፡፡





ምስል 1.16፡ የዱር እንስሳት

## ረ. የተለያዩ የማጓጓዣ አይነቶች

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- በአከባቢያችሁ የሚገኙ የተለያዩ የማጓጓዣ ዓይነቶች ዘርዝሩ?
- የየብስ፣የአየር እና የባህር የማጓጓዣ ዓይነቶች ዘርዝሩ?




ምስል 1.17: የተለያዩ የማጓጓዣ አይነቶች

የማጓጓዣ ዓይነቶች በሦስት ይከፈላሉ እነሱም የየብስ፣የባህር እና የአየር መጌጌዣ ይባላሉ።

የየብስ ማጓጓዣ የሚባሉት እንደነ መኪና፣ሞተር ሳይክል ፣ባስ፣ባጃጅ፣ፈረስ፣ግመል ወ.ዘ.ተ. ናቸው።

- የባህር ማጓጓዣ የሚባሉት ጀልባ፣መርከብ ናቸው።
- የአየር ማጓጓዣ ደግሞ አውሮፕላን፣ጀት፣ፓራሹት ወ.ዘ.ተ. ናቸው።

## መልመጃ 1.5

ሀ. የሚከተለትን ጥያቄዎች በማብራራት መልሱ።

1. አልባሳት ከምን ይዘጋጃሉ?
2. ከ አፈር የሚሰሩ የቤት ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ?

3. በአከባቢያችሁ የሚገኙ የእንጨት ውጤቶችን ዘርዝሩ?
4. የዱር እንስሳት የሚባሉት እነማን ናቸው?
5. የቤት እንስሳት የሚባሉት እነ ማን ናቸው?
6. ከ ቤት እንስሳት ምን ምን አገልግሎት እናገኛለን?

**ለ. የሚከተለትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።**

1. ፈረስ የማጓጓዣ ዓይነት ነው።
2. ጀልባ የየብስ ማጓጓዣ ዓይነት ነው።
3. አውሮፕላን የባህር ማጓጓዣ ዓይነት ነው።

## ሰ. ባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያዎች


**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- በአከባቢያቹ የሚገኙ  የሙዚቃ መሳርያዎች ዘርዝሩ?
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያ ዓይነቶች ዘርዝሩ?
- ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያ ዓይነቶች ዘርዝሩ?

### ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በተለያዩ ማህበረሰቦች ደስታቸውን፣ ሀዘናቸውን፣ አንድነታቸውን ለመግለፅ የሚጠቀሙባቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው።ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በሀገራችን ሰዎች ለሰርግ፣ ለለቅሶ እና በደቦ ስራ ወቅት ይጠቀሟቸዋል።ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሶስት አይነት ናቸው።እነዚህም


1. የክር መሳረያዎች፡ ከተለያዩ ክሮች የሚሰሩ ናቸው ለምሳሌ፡ ክራር፣ ማሲንቆ ወ.ዘ.ተ. ናቸው።
2. የትንፋሽ መሳሪያዎች፡ በትንፋሽ የሚሰሩ መሳሪያዎች ናቸው። ለምሳሌ፡ ዋሽንት፣ ዲንኬ፣ ሂጺጼ፣ ዛዬ፣ ፊላ ወ.ዘ.ተ. ናቸው።
3. የምት መሳረያዎች፡ በቆዳ እና ከብረት ነክ ቁሶች የሚሰሩ መሳሪዎች  ናቸው። ለምሳሌ፡ ከበሮ፣ አታሞ ወ.ዘ.ተ. ናቸው።




ምስል 1.18፡ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

## ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

በአለማችን በርካታ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አሉ፡፡እነዚህም ኪቦርድ፣ ትራምፔት፣ ሀርሞኒካ፣ ድራም፣ ፍሉት፣ ቫዮሊን ወ.ዘ.ተ.ናቸው፡፡





ምስል 1.19፡ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያዎች

## ቀ. የብርሃን ምንጮች

ብርሀን ጨለማን በመገርሰስ ነገሮችን እንድንመለከት ያደርገናል፡፡ብርሀን በተለየያ መንገድ ሊገኝ ይችላል፡፡የብርሀን ምንጮችን ሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ የሚገኙ ብለን ለሁለት እንከፍላቸዋለን፡፡

ተፈጥሮአዊ የብርሀን ምንጮች፡ የምንላቸው- ፀሀይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት ናቸው፡፡

ሰው ሰራሽ የብርሀን ምንጮች፡ የምንላቸው-አንፖል፣ የእጅ ባትሪ፣ ክብሪት፣ ሻማ፣ ማቀጣጠያ እና እሳት ናቸው፡፡




ምስል 1.20፡ የተለያዩ የብርሃን ምንጮች

## መልመጃ 1.6

1. ባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያዎች ዘርዝሩ?
2. የክር አና የትንፋሽ የሙዚቃ መሳርያዎች ዘርዝሩ?
3. ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ የብርሀን ምንጮች ዘርዝሩ?

## 1.5. የእለት ተእለት ማህበረሰባዊ ክንዋኔዎች

### መግቢያ

ተማሪዎች፡ የእለት ተእለት ማህበረሰባዊ ክንዋንዎች የምንላቸው በየቀኑ የምንተገብራቸው ክንዋኔዎች ናቸው፡፡ለምሳሌ፡- ገበያ፣ማንበብ፣ጽዳት መጠበቅ፣አብሮ መመገብ፣መጫወት ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡

**ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የእለት ተእለት ማህበረሰባዊ ክንዋኔዎችን የሚያሳዩ ምስሎች ትረዳላችሁ፡፡



ምስል 1.21፡ እናት እንጀራ ስትጋግር

### ሀ. የአመጋገብ ሰርዓት

በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ የአመጋገብ ሥርዓቶች አሉ፡፡ አመጋገባችን እንደየ ባህላችንና እንደየሥልጣኔያችን ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በገጠርና በከተማ በሚኖሩ ሰዎች የአመጋገብ ልምድና ለመመገቢያ የሚጠቀሙባቸው ዕቃዎች ተመሳሳይ አይደሉም፡፡



ምስል 1.22፡ የአመጋገብ ሥርዓት

## ለ. ንጽህናን መጠበቅ

አበበ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡ጠዋት ከእንቅልፉ እንደተነሳ ፊቱን ይታጠባል ፣ጥርሱን ይቦርሻል፣ ጸጉሩን ያበጥራል የራሱን ንጽህና ከጠበቀ በኋላ የተኛበትን አልጋ በማንጠፍ ቤቱን እና አከባቢው በመጥረግ ንጽህና ይጠብቃል፡፡

- የቤትንና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ሁል ጊዜ ያስፈልጋል፡፡
- የቤትንና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ከበሽታ ይከላከለናል፡



ምስል 1.23፡ ልጆች አካባቢያቸውን ሲያፀዱ

## ሐ. እጽዋትን መንከባከብ

አበባና አበበ የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አበበ እጽዋትን መትከል ይወዳል፡፡አበባ ደግሞ አበበ የተከላቸውን እጽዋቶች ውሀ በማጠጣት ትንከባከባቸዋለች፡፡አበባና አበበ በትምህርት ቤታቸው የተለያዩ የእጽዋት አይነቶችን በመትከል የትምህርት ቤቱን ጊቢ ጽዱና ማራኪ እንዲሆን አድርገዋል፡፡

- እጽዋትን እና ችግኞችን በትምህርት ቤት መትከል ለትምህርት ቤቱ ውበት ይሰጣል፡፡
- እጽዋትን እና ችግኞችን መትከል አከባቢያችንን እንዲጠበቅ እና መሬቱ በጎርፍ እንዳይሸረሸር ይጠቅማል፡፡



ምስል 1.24፡ ልጆች በጋራ ችግኝ ሲተክሉ

## መ. የማንበብ ልምድ

ተማሪዎች ወደ ቤተ መጻሕፍት በመሄድ መጻሕፍትን ጋዜጦችንና መጽሔቶችን በማንበብ ብዙ ዕውቀት እናገኛለን፡፡

ማንበብ እወዳለው
ማንበብ እወዳለው
ሁልጊዜ አነባለው
ባነበብኩኝ ቁጥር
ይገባኛል ሚስጥር(2)
የጥበብን ሚስጥር
እኔ ልንገራችሁ
በየመፅሀፍቱ ታገኝታላቹ



ምስል፡ 1.25 ተማሪዎች በቤተ መጻሕፍት ጥናት ሊይ

## ማጠቃለያ

- በመጀመሪያ ኖታ የምንለው የሙዚቃ ፊደላትን ነዉ፡፡ ሙሉየሙዚቃ ኖታ በውስጡ 4 ምት ያለው ሲሆን በጊዜ ዋጋ ከሁለት ግማሽ ኖታዎች ጋር እኩል ነው፡፡ግማሽ የሙዚቃ ኖታ ማለት ሁለተኛው የኖታ ዓይነት ሲሆን በውስጡ ሁለት ምት አለው፡፡
- የቤትንና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ከበሽታ ይከላከለናል፡፡
- የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎችን ለመጎብኘት ብዙ የውጭ ዜጎች ስለሚመጡ እነደ ገቢ ምንጭ ሆኖው ያገለግላሉ፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

### ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ

1. ሙሉ የሙዚቃ ኖታ ___________ አለዉ
   ሀ. አራት ምት
   ለ. አራት ዕረፍት
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ
2. የአየር መጓጓዣ የሆነዉ የቱ ነዉ
   ሀ.አዉሮፕላን   ለ. ታክሲ   ሐ. ጀልባ
3. ከሚከተሉት ዉስጥ የህፃናት ጨዋታ የሆነዉ የቱ ነዉ
   ሀ. ማረቤን ያያችሁ
   ለ.ድንቢ ለድንቢ
   ሐ.ሁሉም መልስ ነቸዉ

### ለ. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ

1. የዕደ-ጥበብ ውጤቶችን ዘርዝሩ?
2. የዱር እና የቤት እንስሳት የሚባሉ እነማን ናቸው?
3. የተለያዩ የማጓጓዣ አይነቶችን ጥቀሱ?

### ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ

1. ሙዚቃ እንቅስቃሴዎችን ከውዝዋዜዎች ጋር እያዛመዱ የሚተገብሩበት መንገድ ነው፡፡
2. ቀለል ያሉ እንቅስቃሴዎችንና ውዝዋዜን ህጻናት እያደረጉ የራሳቸውን አዕምሮ የሚያድሱበት ዘዴ ነው፡፡




## መግቢያ

ተማሪዎች ንድፍ ተጠቅማቹ ሃሳባቹን ስሜታቹን ባጠቃላይ ማለት የምትፈለጉትን ነገር መግለፅ ትችላላቹ፡፡ሰለዚህ ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ የሚሰጡ ትምህርት እና መልመጃዎች በአግባቡ በመስራት የንድፍ ችሎታችሁን አዳብሩ፡፡

### ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የሙዚቃ ኖታዎችን ተጠቅማችሁ የተለያዩ ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ
- ቀላል የትወና ጨዋታ ትጫወታላችሁ
- ቀላል መስመሮች ተጠቅማችሁ አከባቢያችሁ ላይ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በወረቀት ላይ ትስላላችሁ

## 2.1. የሙዚቃ ኖታዎችን መጫወት

### መግቢያ

የሙዚቃ ኖታዎችን መጫወት ስንል በምዕራፍ አንድ የተመለከታችሁትን የሙዚቃ ኖታዎች በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የተለያዩ ምልክቶችን በመጠቀም ቀስ በቀስ ወደ ማንበብ መሄድ ነዉ፡፡

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ፡-


- የሙዚቃ ኖታዎችን ተጠቅማችሁ የተለያዩ ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ
- የሙዚቃ ኖታዎችን አጻጻፍ ትገልፃላችሁ
- የሙዚቃ ኖታዎችን ትለማመዳላችሁ

### ማነቃቂያ (መሪ ተግባራት)


- ተማሪዎች፡ የሙዚቃ ኖታዎችን ማጫወት ምን እንደሆነ አብራሩ፡፡


ሙሉ የሙዚቃ ኖታ እና ሌሎችንም የሙዚቃ ኖታዎች እና የእረፍት (ድምፅ አልባ) የሙዚቃ ምልክት እንዴት በምልክት ማንበብ እንደምንችል እንመለከታለን፡፡ለኖታዎቹ ምልክት ስንጠቀም ያልተቆራረጠ መስመር ሲሆን በአንድ ትንፋሽ (ሳይቆራረጡ) በጭብጨባ ወይም በእግር መሬት እየመቱ ማንበብ ሲሆን ወደ ዕረፍት ምልክት ስንመጣ ደግሞ ምልክቶቹን በተቆራረጠ መስመር ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ የዝምታ ዋጋቸውን በማወቅ በዝምታ ማለፍ፡፡





አራት ጊዜ ማጨብጨብ | አራት የዝምታ ጊዜ





ሁለት ጊዜ ማጨብጨብ | ሁለት የዝምታ ጊዜ

በዚህ መልክ ሁሉንም የሙዚቃ ኖታዎችን ደጋግሞ በግልና በቡድን በመሆን ማንበብ፡፡

## መልመጃ 2.1

1. የእነዚህን የሙዚቃ ኖታዎች ስም ፃፍ

ሀ. h ____________________

ለ. W ____________________

ሐ. O ______________________________

መ. H ______________________________

ሠ. h ______________________________

2. የእነዚህን የሙዚቃ ኖታዎች የጊዜ ቆይታ በቁጥር ያስቀምጡ

ሀ. h ______________________________

ለ. W ______________________________

ሐ. O ______________________________

መ. H ______________________________

ሠ. h ______________________________

## 2.2. ቀለል ያሉ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ፡-

- ሙሉ ኖታ እና ግማሽ ኖታን  ታነባላችሁ
- የተለያዩ መዝሙሮችን በእንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ትዘምራላችሁ

ለምሳሌ ይህን የልጆች መዝሙር ስንመለከት ደስታቸውን ለመግለፅ የሚያደርጉትን ጭብጨባ፣ዝላይ፣ሳቅ እና የመሳሰሉትን እንቅስቃሴና (ውዝዋዜ) እንመለከታለን፡፡

ደስተኛ የሆነ

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ ቸብቸብ (2x)

ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ ቸብቸብ

ደስተኛ የሆነ ይደንስ ዳንስ ዳንስ (2x)

ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ ይደንስ ዳንስ ዳንስ

ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ ሀ ሀ ሀ (2x)

ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ ሀ ሀ ሀ

ደስተኛ የሆነ ወደ ላይ ይዝለል 2x

ዘለል ዘለል

ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ ወደ ላይ ይዝለል

ዘለል ዘለል

## መዝሙሮች ዘምሩ

ከታች የተፃፈውን መዝሙር በመመልከት በአከባቢያቹ ቋንቋ በመቀየር ዘምሩ

እቴ ሜቴ

እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ
እማ ደጓ ምን አለች ማታ
ምንም (3x) አላለች
ወተቱን አልባ ጠጭልኝ አለች
በላሜቦራ በጡቴ ብላ
በላው ጠገብኩኝ ከእማ ከፍቅሯ

## 2.3. ቀላል የትወና ጨዋታዎችን መጫወት

### መግቢያ

ቀላል የትወና ጨዋታ የምንላቸው በትወና የቤተሰብን ገፀ- ባህሪያት በመወከል እና በመከፋፈል እያስመሰላችሁ ምትጫወበት ነው፡፡

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ፡-

- ቀላል የትወና ጨዋታ ትጫወታላችሁ
- የቤተሰባችሁ ገፀ- ባህሪያት ወክላችሁ ትጫወታላችሁ

እናት አባት ልጅ ተባብለው የአባትን የሚተውነው አባት ከሥራ ሲመለስ ፧ቤት ውስጥ የምናገራቸው የምያደርጋቸው ድርጊቶች እያስታወሱ ይተውናሉ (ያስመስላሉ) አባት ከሥራ ስመጣ እናት ምግብ ታቀርባለች ልጅ እጅ ያስታጥባል መሰል ድርጊቶች በማስታወስ ያስመስላሉ፡፡ ይህ የማስመሰል ጨዋታ አድጎ አለባዊያን ተጨምሮበት

የትወና መንገዶች (ቴክኒኮች) ተጨምረውበት ቴውኔት (ትያትር) ድርስ ያድጋሉ መሰረቱ የማስመሰል የልጆች ጨዋታ ነው፡፡



ምስል 2.1፡ አበበ እንደ አባት አበባ እንደ ልጅ ሆነው ሲተውኑ

## መልመጃ 2.2

1. ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቹ የምትወዱትን የቤተ-ሰብ አባል አስመስላችሁ ተውኑ፡፡
2. ተማሪዎች ቡድን በቡድን በመሆን የእናት የአባት የልጅ ገፀ-ባህሪያትን በመከፋፈል ተውኑ፡፡

## 2.4. ቀለል ያሉ መስመሮች በመጠቀም መቸክቸክ እና የመስመር ንድፎችን መለማመድ

### መግቢያ

ተማሪዎች ንድፍ ተጠቅማቹ ሃሳባቹን ስሜታቹን ባጠቃላይ ማለት የምትፈለጉትን ነገር መግለፅ ትችላላቹ፡፡ስለዚህ ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ የሚሰጡ ትምህርት እና መልመጃዎች በአግባቡ በመስራት የንድፍ

ችሎታችሁን አዳብሩ፡፡

## ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ፡-

1. የተለያዩ የመስመር ዓይነቶች ታውቃላችሁ
2. 2.ቀላል መስመሮች ተጠቅማችሁ አከባቢያችሁ ላይ የሚገኙ ቁሳቁሶች በወረቀት ላይ ትስላላችሁ
3. 3.ባለ ሁለት አውታር ቅርፆችን በመገጣጠም ቀለል ያሉ ስዕሎችን ትስላላችሁ

ንድፍ፡- ማለት እርሳስን ተጠቅመን አንድ መስመር ከሌላ መስመር እየቀጣጠልን ወረቀት ላይ የምንሰራቸው የጥበብ ሥራዎች ንድፍ ይባላሉ፡፡

የመስመር መጀመርያ ነጥብ ነው፡፡ አንድ ነጥብ ከሌላኛው ነጥብ ጋር ስናገናኝ መስመር እንሰራለን፡፡

### ተግባራዊ ክንዋኔ





ስለዚህ ተማሪዎች ስዕል ወይም ንድፍ ለመስራት አንድ መስመር ከሌላ መስመር በመገጣጠም የምንፈልገው አይነት ቅርፅ መስራት እንችላለን፡፡ መስመሮቹን በተለያዩ አቅጣጫዎች በመሥራትና በመገጣጠም የቅርፆቹን ንድፍ እንሰራለን፡፡


መስመሮች በመጠቀም ባለ ሦስት መዓዝን ቅርፅ መስራት

ምሳሌ፡ ባለ ሦስት መዓዝን ቅርፅ ለመስራት እንደሚከተለው ይሆናል።


1. ሰያፍ መስመር እንሰራለን።





2. ከነጥብ "ሀ" ተነስተን ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ሰያፍ መስመር እናሰምራለን።




3. በመጨረሻም ከነጥብ "ለ" ተነስተን እስከ ነጥብ "ሐ" እናሰምራለን።



## መስመሮች በመጠቀም መቸክቸክ




ምስል 2.2፡ መስመሮች በመጠቀም መቸክቸክ




ምስል 2.3፡ ቀላል መስመሮችን በመጠቀም መሳል

ሞገዳማ መስመር በመጠቀም ደመና፣ወንዝ፣ሀይቅ እና ጎርፍ፤የተቆራረጠ መስመር በመጠቀም ዝናብ እና ዚግዛግ መስመር በመጠቀም ተራራ መስራት እንችላለን።




ምስል 2.4፡ መጎዳማ መስመር በመጠቀም ወንዝ(ማዕበል)መሳል

## መልመጃ 2.3


1. አግድምና ቁልቁል ቀጥታ መስመሮችን በወረቀት ላይ አስምሩ?
2. የተለያዩ መስመሮችን ተጠቅማችሁ ወደ ብዙ አቅጣጫ ችክችኩ?

## የተለያዩ የመስመር አይነቶች




ምስል 2.5፡ የተለያዩ የመስመር አይነቶች

| የተለያየ ውፍረት እና እጥፋት ያላቸው የመስመር አይነቶች |
|---|



ምስል 2.6፡ የተለያዩ የመስመር አይነቶች


የምንፈልገው አከባቢያችን ላይ የሚገኙ ቁሶች ለመሳል ከላይ የቀረቡትን የተለያዩ ውፍረት እና እጥፋት ያላቸው የመስመር አይነቶች በመጠቀም በቀላል መንገድ የፈለግነው ንድፍ ለመስራት ያስችሉናል።

እርሳስ በመጠቀም በእጃችሁ ቀጥታ መስመር ወደታችና ሰያፍ መቸክቸክ እንችላለን።







## መሰረታዊ ዝርግ ቅርፆች

ተማሪዎች ከላይ ባየነው ምሳሌ መሰረት ዝርግ ቅርፆች መስራት እንችላለን::





ምስል 2.7፡ የተለያዩ የዝርግ ቅርፅ አይነቶች


<table>
<tr><th colspan="2">የነጥብ እና ክብ ቤተ-ሰብ</th></tr>
<tr><td rowspan="2"></td><td></td></tr>
<tr><td>የነጥብ ቤተ-ሰብ እና ሞላላ ሲሆኑ ውስጣቸው የተቀቡ ናቸው</td></tr>
<tr><td rowspan="2"></td><td></td></tr>
<tr><td>የክብ(ሰርክል) ቤተ-ሰብ ሞላላ ሲሆኑ ውስጣቸው ያልተቀቡ ናቸው</td></tr>
</table>

ምስል 2.8፡ የተለያዩ የክብ አይነቶች


ተማሪዎች አሁን ደግሞ ዝርግ ቅርፆች እርስ በእርስ በማቀላቀል አከባቢያችን ላይ የምንመለከታቸውን ቁሳቁሶች እንሰራለን፡፡



ምስል 2.9፡ ዝርግ ቅርፆች እርስ በእርስ በመገጣጠም ታክሲ መሳል




ምስል 2.10፡ ዝርግ ቅርፆች እርስ በእርስ በመገጣጠም ክራር መሳል




ምስል 2.11፡ ዝርግ ቅርፆች እርስ በእርስ በመገጣጠም ጎጆ ቤት መሳል


ተማሪዎች በክልላችን ደቡባዊ የኢትዮጵያ ክፍል ከሚገኙ የውሃ ውስጥ ሃብቶች አንዱ ዓሳ ነው፡፡


ከታች በምንመለከተው ሰንጠረዥ ዓሳን በቀላል መስመሮች እና ቅርፆች በመገጣጠም እንዴት እንደሚሰራ ተመልከቱ፡፡



| | |
|---|---|
| 4 |  |
| 5 |  |

ምስል 2.12፡ በቀላል መስመሮችን እና ቅርፆችን በመገጣጠም ዓሣ መሳል





ምስል 2.13፡ በቀላል መስመሮች እና ቅርፆች በመገጣጠም ደሮ መሳል

## ማጠቃለያ

- ሙሉ የሙዚቃ ኖታ እና ሌሎችንም የሙዚቃ ኖታዎች እና የእረፍት (ድምፅ አልባ) የሙዚቃ ምልክት እንዴት በምልክት ማንበብ እንደምንችል እንመለከታለን ሁሌም ልጆች ከእንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ጋር የተቆራኙ ናቸው። ማለትም ልጆች ማንኛውም ነገር ለመግለፅም ሆነ ለመረዳት በእንቅስቃሴ (ውዝዋዜ) ሲሆን ቶሎ የመረዳት አቅም አላቸው።
- የመስመር መጀመርያ ነጥብ ነው። አንድ ነጥብ ከሌላኛው ነጥብ ጋር ስናገናኝ መስመር እንሰራለን።
- ንድፍ ማለት እርሳስን ተጠቅመን አንድ መስመር ከሌላ መስመር እየቀጣጠልን ወረቀት ላይ የምንሰራቸው የጥበብ ሥራዎች ንድፍ ይባላሉ።

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. ሙሉ የሙዚቃ ኖታ እና ግማሽ የሙዚቃ ኖታን ከነ የእረፍት ምልክታቸዉ ያሳዩ
2. ንድፍ ማለት ምን ማለት ነው?
3. ንድፍ ለመስራት የሚስፈልጉ ግብአቶች ዘርዝሩ?
4. መስመር ማለት ምንድን ነው?
5. የመስመር ዓይነት የሆነዉ የቱ ነዉ

   ሀ. አግድም መስመር

   ለ. ቁልቁል መስመር

   ሐ. ሁሉም መልስ ናቸዉ
6. የቤተሰቦቻችን ገፀ-ባህሪያት በመምሰል እንዴት መቻጫወት እንችላለን

   ሀ. እናትን በመምሰል

   ለ. አባትን በመምሰል

   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ነቸዉ



# ምዕራፍ 3
## ሀገረ-ሰባዊ ምልከታዎች

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡**

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ፡-
- በአከባቢያችሁ የሰማችሁትን ሙዚቃ እየዘመራችሁ ትወዛወዛላችሁ
- ተዛማጅ ታሪኮችን ከሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ጋር ታዛምዳላችሁ
- ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃንና ውዝዋዜን ትለያላችሁ
- የብሔር ብሔረሰቦችን ሙዚቃ ትጫወታላችሁ
- ቀለማት ከባህላዊ ምልከታ አኳያ ታውቃላችሁ

## 3.1. ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ

### መግቢያ

ሀገረ - ሰባዊ ሙዚቃ ወይም ውዝዋዜ ማለት የአንድ ሀገር ወይም አከባቢያዊ ክንዋኔዎች መግለጫ ነው፡፡ ማለትም አንድ አከባቢ የራሱ የሆነ የሀዘን ፣ የደስታ እና የክብረ በዓላት መግለጫ አላቸው፡፡

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ፡-

- ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ትገልፃላችሁ
- በአከባቢያችሁ የሰማችሁት ሙዚቃ እየዘመራችሁ ትወዛወዛላችሁ
- ተዛማጅ ታሪኮችን ከሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ጋር ታዛምዳላችሁ
- ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃንና ውዝዋዜን ትለያላችሁ
- የብሔር ብሔረሰቦችን ሙዚቃ ትጫወታላችሁ

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ሀገረ - ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ምን እንደሆነ ግለፁ

ሀገረ-ሰባዊ ማለት የአንድ አከባቢ ባህላዊ (እምነት) ማለት ሲሆን ሀገራ-ሰባዊ ሙዚቃ ወይም ውዝዋዜ በአንድ አከባቢ (ሀገር) የሚከናወኑ (የክንዋኔዎች) መገለጫን በሙዚቃ እና በውዝዋዜ በማዋዛት የሚከናወን ነው፡፡ ይህም ስንል በተለያዩ አከባቢ የተለያዩ የባህል (የእምነት) ክብረ-በዓላት አሉ እነዚህም ደቦ ወይም ስዎች ተሰባስበው የአንድን ሰው ቤት፣የእርሻ ቦታ ወዘተ ተሰባስበው በቡድን የሚሰሩት ነው፡፡በዓመት በዓሎች፣ዕረኞች በሚጠብቁበት ቦታ፣በአጠቃላይ በሐዘን እና በደስታ ላይ ሁሉም አከባቢ የየራሳቸው የሆነ በህል አላቸው፡፡አንዳንድ አከባቢዎች በሐዘን ጊዜ ሙዚቃ (ውዝዋዜን) በመጠቀም የሐዘንን ሥነ-ስርዓት እንደ ስዉ የዕድሜ ክልል በሞቱ ምክንያት የተሰማቸውን ሐዘን እየገለፁ ያከብራሉ፡፡ ሁሉም በራሱ

ባህል እና በራሱ እምነት ትክክል ነኝ ብሎ ያመነበትን ያለ አንዳች ፍርሃት እና መሸማቀቅ ያከብሩታል ወይም ይተገብሩታል፡፡ ይህ ማለት አንዳንድ ጎጂ የሆኑ ባህሎችም እንዳሉ ልትገነዘቡ ይገባል፡፡

ለምሳሌ፡- በጋሞ አከባቢ ውስጥ ብቻ የምናገኛቸው ብዙ አይነት አስደናቂ የሀዘን፣የደስታ መግለጫ ክብረ በዓላት ላይ የሚጠቀሙት ሙዚቃዊ ውዝዋዜዎች አላቸው፡፡

ከነዚህም ውስጥ የሀዘን፤የጋራ የሥራ ዘፈኖች እና ደስታ ዘፈኖችን እንመለከታለን፡፡

<u>የበዓል ዘፈኖች</u>፡- በብሄረሰቡ ዘንድ በጣም ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱና ዋንኛው "ዮ ማስቃላ" ሲሆን ጥምቀትም በኦርቶዶክስ እምነት ተከዮች በጣም ከቅድመ ዝግጅት እሰከ መጨረሻው ድረስ ብዛት ያላቸው ሥነ-ሥርዓቶች ሳይዛነፉ (አንዳች ሳይቀር) የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን በመጫወት በዓሉን ይጨርሱታል፡፡

በከባታና ጠምባሮ ዞን ዉስጥ የሚጫወቱት የበዓል ዘፈኖች፡-በላ ሄሌሌ፤መሰሊ ወጋ፤መርሽ ወጋ እያሉ ይጫወታሉ፡፡

<u>የሀዘን ዘፈኖች</u>፡- በለቅሶ ጊዜ በሟች ግለሰብ በር በተለያዩ ትይንቶች ታጅቦ የሚቀርብ ዘፈን ነው፡፡ ዱርሳ፣ግግሾ፣ቦሾ እና ሂርፄ የተባሉ የሀዘን መግለጫዎች ጭፈራዎች እና ዝላልሶና የሆ በመባል የሚታወቁ እንጉርጉሮዎች እንዲሁም በሟች ዕድሜ፣ፆታ እና ማህበራዊ የኑሮ ደረጃ በሚለያይ ሁኔታ ሲታይ ልዩ ያደርገዋል፡፡

በከባታና ጠምባሮ ዞን ዉስጥ የሚጫወቱት የሀዘን ዘፈኖች፡-አዬ ሞረ አዬ ሞረ እያሉ አባቶች የሚያዜሙት ዜማ ነዉ፡፡

<u>የጋራ የሥራ ዘፈኖች</u>፡- በብሔረሰቡ አባላት የዕለት ትዕለት እንቅስቃሴ የሚከወኑ ብዛት ያላቸው ጨዋታዎች ሥራ ዘፈኖች፣በዕድሜ፣በጾታ፣በ ሥራቦታ፣ህጻናትነለማባበል፣እንጨት ለመልቀም ስሄዱ፣ውሃ ለመቅዳት ስሄዱ እና ወዘተ በጋራ በአንድ ድምፅ አልያም አንዱ እያወጣ ሌላው እየተቀበለ በጋራ ይዘፍኑታል በእንዳንዱም ሁኔታዎች የሚዘፈኑ ዘፈኖች

እንደ ቦታው ይለያያሉ ፡፡

በከባታና ጠምባሮ ዞን ዉስጥ የሚጫወቱት የጋራ የሥራ ዘፈኖች፡- ዬኔቤ ዬኔቤ ደገሌ ኦዬቹት በመለት ይጫወታሉ፡፡

ለምሳሌ እነዚህን ምስሎች እንመልከት



ምስል 3.1፡ የቤንሻንጉል አከባቢ የሙዚቃ መሣሪያ



ምስል 3.2፡ የኮንሶ ባህላዊ ጭፈራ



ምስል 3.3፡ የሐመር የሴቶች አለባበስ እና ጭፈራ

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ በሚገኙ የሙዚቃ መሣሪያዎች የተሰራ መዝሙር

እኛም አለን ሙዚቃ


እኛም አለን ሙዚቃ ስሜት የሚያነቃ
ዋሽንታችን ላ ላ ላ ላ ላ
ካሳችን ላ ላ ላ ላ ላ
ድንኪያችን ፓምፓምፓምፓምፓም
አታሞችን ድንድንድንድን
ሎላታችን ላ ላ ላ ላ ላ



ምስል 3.4፡ ሎላታ



ምስል 3.5፡ ካሳ



ምስል 3.6፡ ዋሽንት




ምስል 3.7፡ አታሞ

## ተረት ተረት (ሞኙ ቀበሮ)

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ቀበሮ አንድ ትንሽ ግልገል አየና ቀስ ብሎ ወደ እሷዋ ተጠጋና ለግልገሉ እግሯን አስሮ ለመብላት ሲል "እኔን ልትበላኝም ልትገለኝም ትችላለህ የእኔ የመጨረሻ ቃል እባክህ ስማኝ" አለችው፡፡ "ያንቺ ቃል ምንድ ነው?" በማለት ጠየቃት፡፡ እሷዋም "እባክህ አንተ

ዋሽንት ብትጫወትልኝ ደስ ብሎህ ትበላኛለህ" በማለት ነገረችው፡፡እሱም ደስ ብሎት ዋሽንቱን በማምጣት አንተ ዋሽንቱን በሚትጫወትበት ጊዜ በጣም ደስ ይላል አለችው ያሞኝ ቀበሮ ዋሽንቱን ድምፁን ከፍ በማድረግ መንፋት ጀመረ የዋሽንቱን ድምፅ የሰማው የበግ ጠባቂ የራሱን ሁለት ውሻዎችን ጠራቸው ውሻዎችም ያ ሞኝ ቀበሮ ያለበት ደርሶ ግልገሏዋን ከሞት አተረፉዋት፡፡ብልህና ብልጥ የሆነች ግልገል እየተደሰተችና እየሳቀች ተመለሰች፡፡



የዚህ ተረት ቁም ነገር በዚህ ዘመን ብልህና ቁም ነገኛ መሆን እንዳለብን ይገልፃል፡፡

## መልመጃ 3.1

1. ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ ወይም ውዝዋዜ ማለት ምንማለት ነው?
2. ሀገረ-ሰባዊ ማለት ምን ማለት ነው?
3. በአከባቢያችሁ በሃዘን ጊዜ የምጠቀሙት የሙዚቃ መሣሪያ ግለፅ፡ ፡
4. በደቡብ ብሄር ብሔርሰቦች ውስጥ በሚገኙ የሙዚቃ መሣሪዎች የተሰራ መዝሙር በሚለው የግጥሙን ርዕስ ግለፅ፡፡
5. ለግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት
6. ሞኙ ቀበሮ ለመብላት ያለው ማንን ነው?

7. ትንሽ ግልገል ምን ዓይነት ጥያቄ አቀረበች?
8. ሞኙ ቀበሮ የተጠቀመውን የሙዚቃ መሣሪያ ግለፅ
9. የዚህ ተረት ዋና ዓላማ ምንድነው?

## 3.2. ተዛማጅ ታሪኮች

### መግቢያ

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ በአካባቢያችሁ ካሉ ታሪኮች በመነሳት ታሪክ እንድታውቁ የተለያዩ ታሪኮችን በማንበብ እና በማዳመጥ ወይም ፎቶግራፎችንና ስዕሎችን በማየት ታሪኮችን የማወቅ ዝንባሌ እና ፍላጎቱ እንዲኖራችሁ ተዛማጅ ታሪኮች ከአካባቢያችን እስከ ሃገራችን ድረስ ያሉ በየዘመኑ የተከናወኑ ክንዉኖች፣ በተለያዩ ሙያዎች የተሰማሩ የታዋቂ ሰዎች፣የሀገርና ፣የቦታ ስሞችን ወዘተ ማዋቅ አለባቹ፡፡

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ፡-

1. አከባብያዊ ጥበቦችን በመጠቀመም መዝሙሮች፣የተውኔት ገጸበህርያት ታውቃላችሁ
2. ተዛማጅ ታሪኮች እና ተረቶችን ታውቃላችሁ

### የእርቅ ስነ-ስርዓት

በጋሞ ዞን የሚኖሩ ማህበረሰቦች የራሳቸው የሆነ ባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዐት አላቸው፡፡በደል ያደረሰው አካል ለሀገር ሽማግሌዎች ስለ ችግሩ ያስረዳል፡፡የሀገር ሽማግሌዎችም ዱቡሻ በሚባል አደባባይ ላይ የበዳይ እና ተበዳይ ወገንን ይሰበስባሉ፡፡የሀገር ሽማግሌዎች ፃምፓራ የሚባል ጦር መሳይ መሳሪያ በማቆም እረጥብ ሳር ይዘው የተበዳይ ወገንን ለእርቅ ይጠይቃሉ ፡፡የእናንተ መበደል የእኛም በደል ነው ታሳ ታና ሞ እኔን እርቅ ማውረድ ደግሞ ከጥንት አባቶቻችን የወረስነው ባህል ነው እባካችሁ እርቁን ተቀበሉ ብለው ይማጸናሉ፡፡ተበዳዮችም ለሽማግሌዎቹ እሺ እርቁን እንቀበላለን ብለው ይገልጻሉ፡፡ከእርቁ በኃላ በበዳይ ቤት ለተበዳዮች ግብዣ

ያደርጋሉ። በዳይና ተበዳይም በአንድ ቅል ፋርሶ ወይም ቦርዴ ይጠጣሉ በማሃላቸውም ሰላም ይወርዳል።

1. ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ቀለማት እና ትወና ከባህላዊ ምልከታዎች አኳያ

## መግቢያ

ማህበረሰብ ማለት በአንድ አከባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ሲሆኑ ተመሳሳይ የሆነ የኣመጋገብ ስርዓት፣የባህል፣የቋንቋ፣የአለባበስ ስርዓት፣የኑሮ ሁኔታ ወ.ዘ.ተ.የሚጋሩ ህዝቦች ናቸው።

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ የምንመለከተው በማህበረሰብ ውስጥ ያለው ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ቀለማት እና ትወና ከባህላዊ ምልከታዎች ኣኳያ የሚለውን ነው።

## ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ፡-

- የአከባቢያችሁን ባህልና ወግ ትለያላችሁ
- እንደ አከባቢያችሁ ባህልና ወግ ሙዚቃን ተጫወታላችሁ
- ቀለማትን ከባህላዊ ምልከታ አኳያ ታውቃላችሁ
- የቀለም አይነቶችን ታውቃላችሁ
- የቤተሰቦቻችሁ፣የጋደኞቻችሁ የልብስ ቀለማት እና የሀገራችሁ የክልላችሁ የሰንደቅ አላማ ቀለማትን ለይታችሁ ታውቃላችሁ

## 3.3.1 ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ከባህላዊ ምልከታ አኳያ

### የማነቃቂያ ጥያቄዎች

- በአከባቢያችሁ ስላለው የሙዚቃ እና ውዝዋዜ ባህላዊ ምልከታ ምን እነደሚመስል ግለፁ?

ሁሉም ማህበረሰብ በደስታም ፣ በሐዘንም ወይም በተለያዩ ክብረ-በዓላትም ላይ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ልጠቀሙት ይችላሉ። ሲጠቀሙት ግን ሁሉም በራሳቸው ወግ እና ባህልን በጠበቀ አኳያ ነው፡

ሙዚቃ እና ውዝዋዜ በተለያዩ ማህበረስብ ከባህላዊ ምልከታ አንፃር ስንመለከት ሁሉም ሙዚቃን እንደ እምነታቸው እንደ አከባቢያቸው ባህልና ወግ የሁሉም አጠቃቀም የተለያ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ሁሉም ማህበረሰብ የራሳቸው የአለባበስ ሥራዓቶችን በመጠቀም የሙዚቃ መሣሪያዎችንም በመያዝ ውዝዋዜ እና እንቅስቃሴ የሚያሳዩበት ተግባር መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡

## 3.3.2 ቀለማት ከባህላዊ ምልከታ አኳያ

ሰዎች ቀለሞችን ተጠቅመው ደስታቸውን፣ ሀዘናቸውን ወይም ስሜታቸውን ይገለፃሉ፡፡

ቀለማት እንደየማህበረሰቡ የተለያየ አመለካከት እና ትርጉም አላቸው፡፡

ለምሳሌ፡ በአንድ አከባቢ ጥቁር ቀለም የሃዘን መገለጫ ሲሆን በሌላኛው ማህበረሰብ ደግሞ ጥቁር ቀለም የደስታ ወይም የጥሩ ነገር ተምሳሌት ሁኖ ልናገኘው እንችላለን፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች ቀለማት እንደየባህሉ እና እንደየማህበረሰቡ የተለያየ ትርጉም እና አመለካከት    አላቸው፡፡

### መልመጃ 3.2

1. የለበሳችሁት የልብስ ቀለም ምን እነደሆነ ለአስተማሪያቹ ግለፁ?
2. የምትወዱት የቀለም ዓይነት ምነድነው?

1. አከባቢያቹ ላይ በብዛት ምን ምን ዓይነት ቀለሞች ተመለከታቹ?



ምስል 3.8፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

- አረንጓዴ: ለም መሬት እና እድገት
- ቢጫ: ብሩህ ተስፋ፣ፍቅር
- ቀይ: የአባቶቻችን ደም፣ነፃነት እና እኩልነት

በጌጣጌጥ፣በአልባሳት፣የቤት ቀለም እና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች በተለያየ መንገድ ቀለሞቹ ይገባሉ፡፡




ምስል 3.9: በጌጣጌጥ ላይ የሚገኙ




ምስል 3.10፡ የቤት ቀለሞች

## የቀለም አይነቶች

ቀለሞች በአይናችን በማየት እንለያቸዋለን፡፡ቀለም ለማየት ብርሃን ያስፈልገናል፡፡ብዙ የቀለም አይነቶች አሉ እነዚህም ቀይ፣ሰመያዊ፣ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ብርቱካንማ፣ወይንጠጅ፣ሃምራዊ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡





ምስል 3.11፡ የተለያዩ የቀለም አይነቶች




ቀይ ቢጫ ሰማያዊ አረንጓዴ


## የልብስ ቀለም መለየት



ቀይ



ሰማያዊ



ብርቱካንማ




ቢጫ

ምስል 3.12፡ አበባ እና አበበ የተለያዩ የልብስ ቀለሞች ለብሰው




ብርቱኳንማ



ቢጫ



ቀይ



አረንጓዴ

ምስል 3.13፡ የተለያዩ የፍራፍሬ ቀለሞች

## መልመጃ 3.3

1. አቮካዶ ምን አይነት ቀለም አለው?
2. ሰማይ ምን አይነት ቀለም አለው?
3. አበባ እና አበበ ምን አይነት ቀለም ለበሱ?
4. የቀለም አይነቶች ዘርዝሩ?
5. ብርቱካን ምን አይነት ቀለም አለው?
6. ሙዝ ምን አይነት ቀለም አለው?
7. አፕል ምን አይነት ቀለም አለው?

## ባህላዊ የቀለም አዘገጃጀት

ተማሪዎች ኣከባቢያችን ከሚገኙ ቁሳቁሶች እና ተፈጥራዊ ግብአቶች በመጠቀም የተለያዩ ቀለሞች ማዘጋጀት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ እንዴት እንደሚዘጋጅ ተመልከቱ፡፡

1. አረንጓዴ ቀለም አዘገጃጀት

| የቀለም ዓይነት | የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|
| አረንጓዴ ቀለም | • ሙቀጫ (መፍጫ)<br>• አንድ ጎድጓዳ ሳህን<br>• የሻይ ብርጭቆ<br>• ብልቃጥ |

አረንጓዴ ቀለም ከተለያዩ አረንጓዴነት ካላቸው ቅጠላቅጠሎች ማዘጋጀት እንችላለን፡፡

**አሰራር**

1. መጀመርያ ያዘጋጀነውን የብሳና ቅጠል እንወቅጠዋለን፡፡
2. የተወቀጠውን ቅጠል በሳህን ውስጥ አድርገን በትንሹ ውሃ በመጨመር እንፈጨዋለን፡፡
3. የውሃውን መጠን በአንድ ተኩል የሻይ ብርጭቆ በማድረግ የተወቀጠ ቅጠል ላይ ሩብ(1/4) ብርጭቆ ውሃ በመጨመር እናማስለዋለን፡፡

ተማሪዎች በዚህ ሁኔታ የተዘጋጀው ቀለም ስዕል ልንስልበት እና ልንፅፍበት እንችላለን፡፡

2. ቢጫ ቀለም አዘገጃጀት

| የቀለም ዓይነት | የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|
| ቢጫ ቀለም | • ሙቀጫ (መፍጫ)<br>• አንድ ጎድጓዳ ሳህን<br>• መቁረጫ<br>• የመቅመቆ ስር |

## አሰራር

1. የመቅመቆ ሰሩን በደንብ ማጠብ
2. ካጠብነው በኋላ የላይኛው የመቅመቆ ሽፋኑን በቢላዋ እንልጠዋለን፡፡
3. ከላጥነው በኋላ አድቅቀን በመክተፍ ፀሃይ ላይ እናደርቀዋለን፡፡
4. በፀሃይ የደረቀው የመቅመቆ ስር እንወቅጠዋለን፡፡
5. ድስት ለይ ውሃ በመጣድ ሲንተከተክ የተፈጨውን መቅመቆ ስር ድስት ለይ በመጨመር እንዳይጓጉል በደንብ እናማስለዋለን፡፡
6. ከተጣደበት አውርደን ከቀዘቀዘ በኋላ ቀለል ያሉ ስዕሎች መሳል እና ማቅለም እንችላለን፡፡

3. ቀይ ቀለም አዘገጃጀት

| የቀለም ዓይነት | የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|
| ቀይ ቀለም | • ሙቀጫ (መፍጫ)<br>• አንድ ጎድጓዳ ሳህን<br>• ስካር(ሙጫ)<br>• ቀይ አፈር |

## አሰራር

1. አከባቢያችን ላይ ቀይ አፈር በመፈለግ እናዘጋጃለን፡፡
2. ቀይ አፈሩን አሰኪልም እንወቅጠዋለን፡፡
3. የተፈጨውን ቀይ አፈር በፈላ ውሃ በመጨመር እናማስለዋለን፡፡
4. ስኳር በመበጥበጥ ከሚፈላው ቀይ አፈር ጋር በደንብ ማማሰል፡፡

## 3.3. ትወና ከባህላዊ ምልከታ አኳያ

### መግቢያ

ትወና የዕለት ተዕለት ኑሮን ለመድረክ በሚመጥን መልኩ ከሽኖ በመድረክ ማቅረብ ነው፡፡ ትወና በገፀ-ባህሪያት ተከፋፍለው የሚተገበሩትን ታሪኮች

ተግባራት ማሳያ ወይም መናገርያ ነው። በዚህም መሰረት የተለያዩ ባህሎችን ሀገረሰባዊ ድርጊቶችን በትወና ማቅረብ ማሳየት መናገር ይቻላል።

ባህላዊ (ሀገረሰባዊ) ድርጊቶች ከትወና ጋር ይመሳሰላል። ይህን ስንል ባህላዊ(ሀገርሰባዊ) ድርጊቶች በአንድ አከባቢ የሚገኝ ማህበረሰብ ወይም ቡድን አምነው ተቀብለው የሚያከናውኑት ድርጊቶች፣እምነቶች ጊዜውን እና ቦታውን በመጠበቅ በየጊዜው የሚከናወኑ ድርጊቶች ናቸው። አንድ ትውልድ ለቀጣዩ ትውልድ ያስቀጥላል ቀደምት አባት አያቶቹ እንደከወኑት እሱም ይከውናል።

ድርጊቶችም ሙሉ በሙሉ በማስመሰል ይከውናሉ። ከማስመሰል በላይ በመሆን ንግግሮችንም በተመሳሳይ እንደቀደምቶቹ እየደጋገሙ ይከውናሉ። ይህም ማስመሰል ወይም መተወን ነው።



ምስል 3.14፡ ልጆች ተረትተረት ሲያዳምጡ

## መልመጃ 3.4

1. ተማሪዎች፡- ተራ-በተራ በአከባቢችሁ የምታውቁትን ተረት ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ሀገረ - ሰባዊ ሙዚቃ ወይም ውዝዋዜ ማለት የአንድ ሀገር ወይም አከባቢያዊ ክንዋኔዎች መግለጫ ነው፡፡
- ሙዚቃ እና ውዝዋዜ በተለያዩ ማህበረሰብ ከባህላዊ ምልከታ አንፃር ስንመለከት ሁሉም ሙዚቃን እንደ እምነታቸው እንደ አከባቢያቸው ባህልና ወግ የሁሉም አጠቃቀም የተለያ መሆኑን እንመለከታለን፡፡
- ትወና የዕለት ትዕለት ኑሮን ለመድረክ በሚመጥን መልኩ ከሽኖ በመድረክ ማቅረብ ነው፡፡
- ቀለሞች በአይናችን በማየት እንለያቸዋለን፡፡ቀለም ለማየት ብርሃን ያስፈልገናል፡፡
- ሰዎች ቀለሞችን ተጠቅመው ደስታቸውን፣ ሀዘናቸው ወይም ስሜታቸው የገልፃሉ፡፡
- ቀለማት እንደየማህበረሰቡ የተለያየ አመለካከት አና ትርጉም አላቸው፡፡

## ማጠቃለያ መልመጃ

1. በአከባቢያችሁ በሃዘን ጊዜ የምጠቀሙበት የሙዚቃ መሣሪያ ግለፁ፡፡
2. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያሉት ቀለማት ትርጉማቸውን ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ**

1. በጋሞ ብሄረሰብ በመስቀል አከባበር ጊዜ የሚዜም ዜማ የቱ ነዉ
   ሀ. አባበአየሽወይ ለ. ዮ-መስቃላ ሐ. መልስ የለም
2. በኢትዮጵይ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ይለዉ ቢጫ ቀለም ምን ይወክላል
   ሀ. ቡሩህ ተሰፋ ሐ. ለም መሬት እና እድገት
   ለ. ነፃነትና እኩልነት
3. ትወና ከባህላዊ ምልከታ አኳያ እንዴት ማስመሰል እንችላለን
   ሀ. ድርጊቶችን ሙሉ በሙሉ በማስመሰል ለ.ድርጊቶችን በከፊል በማስመሰል ሐ. ድርጊት በሌለበት
4. ሰዎች ቀለሞችን ተጠቅመዉ____________ይገልፃሉ
   ሀ. ደስተቸዉን ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸዉ
   ለ. ሀዘነቸዉ




## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የትውን እና የእይታ ጥበባት በመጠቀም አድናቆትን/ ማድነቅን/ መግለፅ ሲሆን በዚህ መሰረት ተማሪዎች ሙዚቃን፣ ስዕልን፣ ውዝዋዜንና ትወናን /ድራማን/ የማድነቅ ችሎታችሁን እንድታዳብሩ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

### ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የትውን እና የእይታ ጥበባትን ምንነት ታዉቃላችሁ፡፡
- የትውን እና የእይታ ጥበባትን በተግባር ሰርታችሁ ታሳያላችሁ፡፡
- የትውን እና የእይታ ጥበባትን ተጠቅማችሁ ተፈጥሮን ታደንቃላችሁ፡፡

## 4.1. የእይታ እና የትወና ጥበብ ክንዋኔዎች

ተማሪዎች በዚህ በምዕራፍ እይታዊና ክውናዊ ጥበባትን እንዴት ማድነቅና በመጠቀም ተማሪዎች ሙዚቃን፣ ስዕልን፣ ውዝዋዜንና ትወናን /ድራማን/ የማድነቅ ችሎታችሁን እንድታዳብሩ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ምዕራፍ ነው፡፡

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ፡-

- ሙዚቃ ለሰው ልጆች ሁሉ ምን እንደሆነ ትረዳላችሁ
- ልጆች የትውን እና የእይታ ጥበብ ክንዋኔዎች ያሳያሉ
- ልጆች ስዕልን በመሳል፣ በመስማት እና በመጫወት አከባቢያችሁን ታደንቃላችሁ

### 4.1.1 በሙዚቃ ማድነቅ


**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- የትውን እና የእይታ ጥበብ ከማህበረዊ ክንዋኔዎች አንፃር ምን እንደሚመስሉ ለመምህራቹ አብራሩ፡፡

ሙዚቃ በልጆች ሕይወት ውሰጥ ወሳኝ እና በሁሉም ደረጃ ልተገበር የሚገባ የክህሎት ትምህርት ነው፡ ልጆች ሙዚቃን በመስማት እና በመጫወት ካደጉ አዕምሮቸው ብህሩ ነዉ፤

ልጆች ከልጅነታቸው ጀምሮ ሙዚቃን በማወቅ ካደጉ ለሙዚቃው ዘርፍ ብዙ ነገሮችን ማበርከት ይችላሉ፡፡

ጨረቃ ድንቡለቃ



ጨረቃ ድንቡለቃ
አዬ ቤት ገባች አውቃ
አዬ ቤት ያሉ ሰዎች
ፈተጉ ፈታተጉ
በቁሪፍቱ አስቀመጡ
ቁሪፍቷ ስትሰበር
በዋንጫ ገለበጡ
አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ
ያችን ትተሽ ይህችን ቶሎ

ገበሬው በእርሻ ቦታ



ገበሬው በእርሻ ላይ ገበሬው በእርሻ ላይ
እዩት ተመለክቱት ገበሬው በእርሻ ላይ
ገበሬው ሚስት አለው ገበሬው ሚስት አለው
እዩት ተመለክቱት ገበሬው ሚሰት አለው
ሚስትየው ልጅ አላት ሚስትየው ልጅ አላት
እዩ ተመከቱ ሚስትየው ልጅ አላት
ልጁ ሞግዚት አለው ልጁ ሞግዚት አለው
እዩ ተመልከቱ ልጁ ሞግዚት አለው
ሞግዝቷ ውሻ አላት ሞግዝቷ ውሻ አላት

እዩ ተመልከቱ ሞግዝቷ ውሻ አላት
ውሻው ድመት አለው ውሻው ድመት አለው
እዩ ተመልከቱ ውሻው ድመት አለው
ድመቷ አይጥ አላት ድመቷ አይጥ አላት
እዩ ተመልከቱ ድመቷ አይጥ አላት
አይጧ አይብ አላት አይጧ አይብ አላት
እዩ ተመልከቱ አይጧ አይብ አላት
አይብ ብቻውን ነው አይብ ብቻውን ነው

እዩ ተመልከቱ አይብ ብቻውን ነው

## ኤሊ እና ጥንቸል



ኤሊ እና ጥንቸል ተነጋገሩ
ማራቶን እሩጫ ልወዳደሩ
ውድድሩ ሲያበቃ ሩጫው
እስኪ ገምቱ የማን ነው ዋንጫው
እነ ጦጦና እነ ዝንጀሮ
እነ ተኩላ እና እነ ቀበሮ

ውድድር ልያዩ ተሰባስበዋል

ኤሊ እና ጥንቸል ተዘጋጅተዋል

ኤሊ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ

ጥንቸልዋ በርቺ በርቺ እንዳትረች

ሽጉጥ ሲቶከስ ጥንቸል በረረች

ኤሊ እንደ አቅሟ ተወተረተረች

ጥንቸል ፈጥና ከዓይን እርቃለች

ድንጋዩ ከብዷት ኤሊ ደክማለች

ጥንቸልዋ በርቺ በርቺ እንዳትረች (2)

ኤሊ ቀርፋፋ መቼም አትቀድመኝ

ትንሽ ልተኛ መቼም አትቀድመኝ

ትንሽ ልተኛ በጣም ደከመኝ

ብላ ብተኛ ስለናቀቻት

ቀረፈፍ እያለች ኤሊ አለፈቻት

ኤልዬ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ (2)

ኤሊ አሸንፋ ገመድ ስትበጥስ

ጥንቸል ነቃች ሕልሟን ሳትጨርስ

ጥንቸል አፈረች አንገቷዋን ደፋች

ባልናኳት ብላ በጣም ተከፋች

ኤልዬ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ (2)

## መልመጃ 4.1

1. በአከባቢያችሁ የሚታወቁ ሙዚቃዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ እየዘመራችሁ አሰሙ።
2. በአከባቢያችሁ አርሶ አደሮች (ገበሬዎች) በሥራ ቦታ የሚዘምሩትን ሁለት መዝሙሮችን ግለፁ።

## መልመጃ 4.2

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ

1. ________ለሰው ልጆች ሁሉ ከሀዘን መውጫ፣በደስታ ጊዜ መዝናኛ ሊሆን ይችላል።

| | |
|---|---|
| ሀ/ ሙዚቃ | ሐ/ ተውኔት |
| ለ/የእይታ ጥበብ | መ/ ሁሉም |

2. ገበሬው በእርሻ ቦታ በሚለው ግጥም ስንት ስንኝ አለው

| | |
|---|---|
| ሀ/ 4 | ሐ/ 5 |
| ለ/ 6 | መ/ 3 |

3. ኤሊና ጥንቸል በ________ሩጫ ተወዳደሩ

| | |
|---|---|
| ሀ/ ማራቶን | ሐ/ሀእናለ |
| ለ/ውሃ ዋና | መ/መልስ የለም |

4. እስኪ ገምቱ የማን ነው ዋንጫው ብሎ የተሰበሰቡት እነማን ናቸው?


| | |
|---|---|
| ሀ/ ጦጣ | ሐ/ተኩላ እና ቀበሮ |
| ለ/ዝንጀሮ | መ/ ሁሉም |

### 4.1.2 ስዕልን በመስራት ማድነቅ


ተማሪዎች አድናቆት ማለት ለአንድ ስራ ወይም ተፈጥራዊ ለሆኑ ነገሮች እውቅና ወይም ምላሽ መስጠት ማለት ነው። አከባቢያችን ላይ ብዙ የሚደነቁ ነገሮች አሉ።

### የማነቃቅያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ለስዕል ያላችሁን አድናቆት በየግላችሁ መምህራችሁ በሚያሳያችሁ መሰረት ስዕል በመስራት አድናቆታችሁን ግለፁ።




ምስል 4.1፡ አበባ ስዕል ስትለማመድ




ምስል 4.2፡ ክብ ቅርፅ በመገጣጠም አበባ መሳል

## መልመጃ 4.3

1. ከላይ በተቀመጠው ምሳሌ መሰረት አበባ ስላችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

### 4.1.3 ትወናን /ድራማን/ ትወና በመስራት ማድነቅ

ተማሪዎች የተለያዩ ጨዋታዎችን የሚጫወቱት በማስመሰል የተለያዩ ገፀ-ባህርያትን ድርጊያዎችን በመጠቀም ስለሆነ በእነዚህ ጨዋታዎች ሳይረዱት ሳያውቁት የተለያዩ ገፀ-ባህርያትን በመውሰደ ይተውናሉ፡፡

ለምሳሌ፡ ዕቃ ዕቃ ሲጫወቱ የአባትን የእናትን የልጅን ወዘተ ገፀ-ባህርያት በመውሰድ በቤታቸው ውስጥ ቤተሰቦቻቸው ሲከውኑ ያዩትን የሰሙትን ያስመስላሉ፡፡ እንደ ሆያ ሆዬ፣አበባዬሽወይ የመሳሰሉ ጨዋታዎችን ደግሞ ግጥም ዜማ እና ድራማዊ ድሪጊታቸውን ጨምሮ የሚከውኑበት ስለሆነ ልጆች በጨዋታ በማስመሰል እና በመተወን ከዚሁ ድርጊት እየተለማመዱ ያጠናሉ ያቀርባሉ፡፡

ሀገሬን ያያችሁ

አጫዋች ፡- ሀገሬን ያያችሁ


ተቀባይ፡- አላየንም ባካችሁ

አጫዋች፡- ሀገሬን ያችሁ

ተቀባይ፡- አላየንም ባካችሁ

አጫዋች፡- ይች የማን ሀገር ናት

ተቀባይ፡- የኔ ሀገር የኔ እናት



ምስል 4.3፡ ልጆች ሀገሬን ያያችሁ ሲጫወቱ

## መልመጃ 4.4

1. ከመጽሐፉ ላይ ያለውን ሀገሬን ያያችሁ የሚለውን ጨዋታ ግጥም ልመዱ::
2. በጨዋታ ቦታ ክብ ሰርታችሁ ተቀመጡ::
3. የለመዱትን ግጥም በማህረቤን ያያችሁ ዜማ ሀገሬን ያያችሁ ብላችሁ ተጫወቱ::

### ማጠቃለያ

- ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ ስዕል፣ ቲያትር እና ፎቶግራፍ የእይታዊና ክዉናዊ ጥበባት ዘርፎች ሲሆኑ ለልጆች ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊና አካላዊ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የኪነ ጥበብ ዘርፎች ናቸው::
- አድናቆት ማለት ለአንድ ስራ ወይም ተፈጥራዊ ለሆኑ ነገሮች እውቅና ወይም ምላሽ መስጠት ማለት ነው::
- ተማሪዎች የተለያዩ ጨዋታዎችን የምጫወቱት በማስመሰል የተለያዩ ገፀ-ባህርያትን ድርጊያዎችን በመጠቀም ስለሆነ በእነዚህ ጨዋታዎች ገፀ-ባህርያትን በመውሰድ መተዎን ነው::
- ሙዚቃ ለሰው ልጆች ሁሉ ከሃዘን መውጫ፣በደስታ ጊዜ መዝናኛ፣ተማሪዎች እያጠኑ እንደ መዝናኛ፣ ሥራዎችን በምንሰራበት ጊዜ እንደ መዝናኛ እና ወዘተ ተግባራትን ለመፈፀም የምንጠቀምበት መሣሪያ ነው::

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምታውቁትን የውዝዋዜ አይነት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ መጫወት አሳዩ፡፡
2. ልጆች በአካባቢያችሁ የምታገኙትን አበባ ንድፍ በየግላችሁ በንድፍና ቀለም በመቀባት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
3. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምታዉቋቸውን የሰዎች ወይም የእንስሳት ድምጽና እንቅስቃሴን አስመስላችሁ በመተወን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡
4. ተፈጥሮን እንዴት ማድነቅ እንችላለን
5. ሽጉጥ ሲተኮስ ጥንቸል በረረች ኤሊ እንደ አቅሟ ________

   ሀ. በረረች　　ሐ. ተውተረተረች

   ለ. ደከመች　　መ. ሁሉም

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ

1. ____________ለልጆች የማህበረዊ፤ ስነ-ልቦናዊና አካለዊ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ የላቸዉ የኪነ-ጥበብ ዘርፎች ናቸዉ

   ሀ . ሙዚቃ　　ሐ. ሀ እና ለ

   ለ. ዉዝዋዜ

2. ____________ማለት ለአንድ ስራ ወይም ተፈጥራዊ ለሆኑ ነገሮች እዉቅና ወይም ምላሽ መስጠት ማለት ነዉ

   ሀ. ቲያትር　　ሐ. ጨዋታ

   ለ. አድናቆት




## መግቢያ

እይታዊና ክውናዊ ጥበባት በአንድም በሌላ መልኩ የራሳቸው የሆነ የእርስ በርስ ዝምድና ያላቸው ሲሆኑ እይታዊ ጥበባት የምንላቸው ሲከወኑ(ሲተገበሩ) በአይን የሚታዩ እንደ ስዕል ፣ቅርጻ ቅርጽ ፎቶግራፍ ወዘተ የመሳሰሉት ሲሆኑ ክዉናዊ ጥበባት የምንላቸው ደግሞ ሲከወኑ(ሲተገበሩ) በአይን የሚታዩ ወይም በጆሮ የሚደመጡ እንደ ሙዚቃ፣ቴያትር( ድራማ)፣ ዉዝዋዜ፣ፊልም፣ትወና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። በመሆኑም በዚህ ክፍለ ትምህርት ስለ እያንዳንዳቸው የእርስ በርስ ዝምድና እንዲሁም ሌሎች ትምህርቶችን ለማስተማር ያላቸውን ሚና እንመለከታለን።

### ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የትውን እና የእይታ ጥበባት ዝምድና ታደንቃላችሁ
- የእይታዊና ክዉናዊ ጥበባትን በተግባር ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።
- የትውን እና የእይታ ጥበባት ዝምድናን ትረዳላችሁ።

## 5.1. ሙዚቃ እና የእይታ ጥበባት ግንኙነት

### መግቢያ

ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ግንኙነታቸውን በዚህ ምዕራፍ በደንብ አድርገን እናያቸዋለን፡፡ ሙዚቃ ማለት ዜማ፣ስልተምት(ሪትም)፣ሃርመኒ(ህብረ ዜማ) ያላቸው ድምፆች ሁሉ ሙዚቃ ለማለት እንችላለን፡፡ የእይታ ጥበብ ማለት መስመሮች ቀለሞች እና ሌሎች ግብአቶች ተጠቅመን የሚሰሩ በአይን የሚታዩ ስዕላዊ መገለጫዎች ሲሆኑ ሙዚቃ እና ስነ-ጥበብ ሁለቱም ለአንድ ማህበረ-ሰብ ሃሳብ እና ስሜቱን በመግለፅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ግንኙነት ትረዳላችሁ
- ስለሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ለማህበረ-ሰብ ያለው አተዋፅኦ ትረዳላችሁ

### ማነቃቂያ ጥያቄዎች

- ተማሪዎች የምታውቋቸውን ሙዚቃዎች በመጫወት ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ አሰሙ?
- ተማሪዎች ስለ ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ግንኙነት እና ልዩነት ግለፁ?

ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ተዛማች እና አንዱ ከአንዱ የማይነጣጠል የትምህርት ዘረፍ ነው፡፡ ሁለቱም ዘርፎች ሰዎች አዕምሯቸውን በመጠቀም የሰውን ስሜት የሚያነቃቁ ነገሮችን ለመፍጥር ይችላሉ፡፡

ሙዚቃ ዜማን፣ስልተምት(ሪትም)፣ህብረ ድምፅ

በመጠቀም የሰውን ስሜትን በማነቃቃት እንዲሁም ሰዎች በአካላቸው እንድንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል፡፡

ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ እርስበርሰ የተሳሰሩ እና ተምሳሌታዊ ናቸው፡፡

አንደ ኪነ ጥበብ ቅርፅ እንከን የለሽ ወደ ሌለ ይለወጣል ሙዚቃ ከጥንት ጀምሮ ለብዙ ሰዓሊዎች እና የእይታ አርቲስቶች ማነቃቂያ እና መነሻ ነው፡፡ ለብዙኃን እንደ መዝናኛ እና ንቁ የጥበብ ተሳትፎ የሙዚቃ ተወዳጅነት በዓለም ውስጥ በሚሊዮኖች በምቆጠር የሙዚቃ ቡድኖች አማካኝነት ይታያል፡፡ እኛ በምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ሙዚቃ ነው ለማለት እንችላለን፡፡

ብዙ ሰዎች በሕልም ውስጥ ሙዚቃን ይሰማሉ እና አንዳንዶች ሙዚቃን ሲሰሙ ቀለሞችን ያያሉ፡፡

### ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ የተለመዱ አካላትን መርሆችን እና ሂደቶችን ያረጋሉ፡፡

| የሙዚቃ አላባዊያን | የእይታ ጥበብ አላባዊያን እና መርህ |
|---|---|
| ዜማ (ሜሎዲ) | እንቅስቃሴ (ሙቨመንት) |
| ስልተምት (ሪትም) | ድግግሞሽ (ሪትም) |
| የድምፅ ንብርብር (ቴክስቸር) | ልስላሴ እና ሸካራነት (ቴክስቸር) |
| አዝማችና ቁጥር መለያ (ፎርም) | ቅርፅ (ፎርም) |
| ቃና (ቲምበር) | ቀለም (ከለር) |
| ህብረ ድምፅ (ሀርመኒ) | ዉበት (ሀርመኒ) |

ሰንጠረዥ 5.1፡ የሙዚቃ እና የእይታ ጥበባት ያለው ዝምድና

## መልመጃ 5.2

### የሚከተሉትን ጥያቄዎችን እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ

1. ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ እርስ በእርስ የተሳሰሩ እና ተምሳሌታዊ ናቸው
2. እኛ በምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ሙዚቃ ነው ለማለት እንችላለን፡፡
3. የሰው አካል የየሙዚቃ መሣሪያ ሊሆን አይችልም
4. በሙዚቃ እና በእይታ ጥበቦች መካከል ብዙ የጋራ ነገሮች አላቸው፡፡

## 5.2. በሰውነት አካላት የሚሰሩ ሙዚቃዎች

### መግቢያ

የሰው አካል የሙዚቃ መሣሪያ ነው።ማለትም የሰውነት አካላችን በማወዛወዝ አስደናቂ የቡድን ሙዚቃን ለመፍጠር ጠቃሚ መሣሪያ ነው።

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ

- የሰውነት አካላት በመጠቀም የተለያዩ ሙዚቃዎችን ትጫወታላችሁ
- በሰውነት አካላት የሚፈጠሩ ድምፆችን ትገልፃላችሁ
- የሰውነት አካላችን በመጠቀም ሪቲምን (ስልተ ምት)ትቆጥራላችሁ
- የሙዚቃ መሣሪያ ሳይኖር ሪቲም (ስልተምት) ጠብቀው እንዴት እንደምትጫወቱ ትገልጻላችሁ
- ልጆች የራሳቸውን የሰውንት አካላት ተጠቅማችሁ የተለያየ ጨዋታዎችን ታሳያላችሁ

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ያለ ሙዚቃ መሣሪያ በሰውነት አካላችሁን በመጠቀም ሙዚቃን ስሩ

በዚህ ክፍል ደረጃ ለሙዚቃ ትምህርት አስፈላጊ የሰውነት አካል ነው። ይህም ማለት የሙዚቃ መሣሪያ ሳይኖር የሰውነት አካላችሁን በመጠቀም ሙዚቃን ሪቲም (ስልተ ምት) ጠብቆ መጫዋት ትችላላችሁ።

ስለምት (ስልተምት) እና ሌሎችን የሙዚቃ ጽንሰ ሀሳቦችን ያስተምራል ማለትም በተለምዶ ዋና ዋና የሙዚቃ ድምፆችን ከዝቅተኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ድምጽ በቀደም ተከተል በእግር መሬትን በመምታት (በመርገጥ) በማጨብጨብ ፣ ጣቶችን ጠቅ ጠቅ በማድረግ ፣የእግር ታፋችንን በእጃችን መታ መታ በማድረግ ፣ ጉንጫችንን በተከፈተ አፍ ማንኳኳት በአፍ ጣሪያ ላይ በምላስ ጠቅ በማድረግ ፣ በማጉረምረም እና በመሳሰሉት ሙዚቃን መሥራት ትችላላችሁ።





ምስል 5.1፡ የተለያዩ የጭብጨባ አይነቶች

## መልመጃ 5.1

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ውስጥ ድምፅ ሊሰጠን የሚችል የሰውነት የሙዚቃ ሪቲም (ስልተምት)

   ሀ/በመርገጥ　　　　ሐ/ ጣቶችን ጠቅ ጠቅ በማድረግ

   ለ/ በማጨብጨብ　　　　መ/ ሁሉም መልስ ናቸው

2. ብዙ ሰዎች በሕልም ውስጥ__________ይሰማሉ፡፡

   ሀ/ ሙዚቃን　　　　ሐ/ ይሮጣሉ

   ለ/ ኳስ ጨዋታን　　　　መ/ ለ እና ሐ

3. አንዳንድ ሰዎች__________ ሲሰሙ ቀለሞችን ያያሉ፡፡

   ሀ/ ጩሀት　　　　ሐ/ ድርሰትን

   ለ/ ሙዚቃን　　　　መ/ መልስ የለም

## 5.3. የእይታ እና የትወና ጥበባት ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ለማገዝ ያለው ጠቀሜታ

### መግቢያ

የትወና እና የእይታ ጥበብ የቋንቋ ትምህርትን በቀላሉ ለማስተማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው። ስነ-ጥበብ በመጠቀም የጤና እና የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት፣የቋንቋ ትምህርት፣የሒሳብ ትምህርት፣የአከባቢ ሳይንስ ትምህርት፣የማህበራዊ ሳይንስ እና ሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማቀናጀት አጋዥ ንድፎች በመስራት ትምህቱ ግልፅ እነዲሆን እና ሀሳባችሁን በቀላሉ እንድትገልፁ ያስችላችኋል በተጨማሪም ሙዚቃ ማለት ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች በሚማሩበት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ እንቅስቃሴና ውዝዋዜ እያደረጉ አዕምሮአቸው የሚያድሱበት ተግባር ነው።

ተማሪዎች ሙዚቃን ከሒሳብ ትምህርት ዓይነት ጋር መቀነስ፣መደመር፣ማባዛት እና ማካፈልን እና የሕሳብ ቁጥሮች በዜማ እንዲማሩ ይረዳል፡በአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ጋር የስሜት ህዋሳት እንድለዩ በሙዚቃ መልክ ማስተማር ያስፈልጋል።

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች ትረዳላችሁ
- ስነ-ጥበብ በመጠቀም የጤና እና የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት፣የቋንቋ ትምህርት፣ሒሳብ ትምህርት፣አከባቢ ሳይንስ ትምህርት፣የማህበራዊ ሳይንስ እና ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማቀናጀት አጋዥ ንድፎችን ትሰራላችሁ

## 5.3.1 ሙዚቃ የአከባቢ ሳይንስ ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ

### የማነቃቂያ ጥያቄ


- ሙዚቃ ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ያለው አስፈላጊነት ምንድን ነው?

ተማሪዎች በቀላሉ ስለ አካባቢያችሁ እንድታዉቁ፣ አካባቢያችሁ ላይ ስላሉ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ስለሆኑ ነገሮች በቀላሉ እንድትረዱ፣ እንዲሁም የግላችሁን፣ የቤተሰቦቻችሁን እና የአካባቢያችሁን ንጽህና ለመጠበቅ የሳይንስ ትምህርትን በስነ ጥበባት ማስተማር የበለጠ እንድትገነዘቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ተማሪዎች እስቲ የሚከተለውን መዝሙር ከሳይንስ ትምህርት ጋር በማዛመድ ዘምሩ፡፡

የስሜት ህዋሳት

አይን አለኝ አያለዉ
ጆሮ አለኝ እሰማለዉ
በአፍንጫዬም አሸታለሁ
በምላሴ እቀምሳለሁ
መዳሰሻም እጅ አለኝ
የስሜት ህዋሴን እወቁልኝ፡፡



ምስል 5.2፡ አምስቱ የስሜት ህዋሳት መዘመር

## ጠንቃቃ ተማሪ

ጥንቃቄን ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ
ሀሳቡን ሰብስቦ መንገድ ተሻጋሪ
የትራፊክ መብራት ሕጎችንም ያውቃል
የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል።
የትራፊክ መብራት ሲያበራ ቀዩን
መኪና ይቆማል ጠብቆ ሕጉን
ወንዝ ስንሻገር ግራ ቀኝ አይተን
መጠንቀቅ አለብን ድልድይ ላይ ሆነን
ጥንቃቄ ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ
ሀሳቡን ሰብስቦ በመንገድ ተሻጋሪ
የትራፊክ መብራት ሕጎችንም ያውቃል
የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል።



### 5.3.2 ሙዚቃ የቋንቋ ትምህርት ለመማር ያለው ጠቀሜታ

ሙዚቃ ከሁሉም የትምህርት ዓይነት ጋር ግኑኝነት እንደለዉ ይታወቃል ከዚህ የትምህርት ዓይነቶች ዉስጥ ከቋንቋ ትምህርት ጋር ያለዉን እንመለከታለን፡፡

ለምሳሌ ፊደላትን ለማወቅ ይሄንን መዝሙር መጠቀም እንችላለን፡፡

እስኪ ልጆች ቺብ ቺብ በእጃችን በሀገራችን ፊደል እስኪ ሀ ሁ እንበል

ሀ ሁ ሂ ምግብ ስንበላ

ረ ሩ ሪ ሁላችንም በጋራ

ኘ ኙ ኚ ፍቅር እንዲደራ

መ ሙ ሚ ኢትዮጵያ ሀገሬ

ነ ኑ ኒ እስኪ ሳቂ ዛሬ

በ ቡ ቢ እኛ አለን ልጆችሽ

ደ ዱ ዲ  አምረን በምድርሽ

ዘ ዙ ዚ ዘላለም ኑሪልን

ቀ ቁ ቂ እኛንም አፍቅሪን

### 5.3.3 ስነ-ጥበብ የጤና እና ሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርትን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ


የጤና እና የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት ለሰዎች አካላዊ፣ ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ይህን ትምህርት የበለጠ ልጆች እንድንገነዘበው ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እንድናደርግ በእይታዊና ክዉናዊ ጥበባት ማስተማር ትምህርቱን አይረሴ ከማድረጉ ባሻገር ልጆች መዝሙሮችን እየዘመርን በነጻነት አካላዊ እንቅስቃሴን እንድናደርግ ያግዘናል ፡፡




ምስል 5.3፡ ቀላል ጨዋታዎች እና የአካል እንቅስቃሴ

## 5.3.4 ስነ-ጥበብ የሂሳብ ትምህርትን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ

እይታዊና ክዉናዊ ጥበባት የሒሳብ ትምህርትን ለማስተማር ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ የቁሳቁሶች ንድፍ እና ይዘት፣ የሒሳብ ምልክቶች እና ቁጥሮችን በስእል እና በሙዚቃ በማስቀመጥ የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡





ምስል 5.4፡ ስዕል በመጠቀም ቁጥር እና ምስል ማዛመድ




ምስል 5.5፡ ስዕል በመጠቀም ቁጥር እና ምስል ማዛመድ

### 5.3.5 ስነ-ጥበብ የቋንቋ ትምህርት ለመማር ያለው ጠቀሜታ


ሀ. የአማርኛ ፊደላትን የአፃፃፍ ስልት መለማመድ



ምስል 5.6፡ ስዕልን ተጠቅሞ ፊደላት እና ቃላት ማስተማር

# ወ

ወንበር



ወንበር

## መልመጃ 5.3

1. ተማሪዎች የአማርኛ ፊደላትን ጥሩ በሆነ የአፃፃፍ ስልት በመፃፍ ቀለም ቀብታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ

### በአማርኛ ፊደላት የሰው ፊት የመሳል ስልት



ፊደል



ደረጃ -1




ደረጃ -2



ደረጃ -3

ምስል 5.7 በአማርኛ ፊደላት የሰው ፊት የመሳል ስልት


## ለ. የእንግሊዝኛ ፊደላትን የአፃፃፍ ስልት መለማመድ



O

orange


orange



F


Fish

Fish



ምስል 5.8፡ ስዕልን ተጠቅሞ ፊደላት እና ቃላት ማስተማር

## በእንግሊዝኛ ፊደላት የሰው ፊት የመሳል ስልት




ፊደል



ደረጃ -1



ደረጃ -2



ደረጃ -2


ምስል 5.9፡ በእንግሊዝኛ ፊደላት የሰው ፊት የመሳል ስልት

### መልመጃ 5.4

1. ተማሪዎች ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ በየግላችሁ የምትወዱትን የእንግሊዝኛ ፊደል ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ
2. ተማሪዎች ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ በየግላችሁ የምትወዱትን የእንግሊዝኛ ፊደል ከጻፋችሁ በኋላ የምትወዱትን ቀለም ቀብታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## 5.3.6 ስነ-ጥበብ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርትን ለመማር ያለው ጠቀሜታ

እይታዊና ክዉናዊ ጥበባት የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር፣ የአመጋገብ ፣ የመረዳዳት በአጠቃላይ የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ልማድ እና እሴት በስዕል ፣በሙዚቃና በቴያትር ለማስተማር ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀገራችንን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የህዝብ አሰፋፈር እንዲሁም ማህበረሰቡ በእለት ከእለት ኑሮው ዉስጥ ስለሚያከናዉናቸው ተግባራት በእይታዊና ክዉን ጥበባት አማካኝነት እንማራለን፡፡



ምስል 5.10፡ አብሮ መመገብ የሚያሳይ ሰዕል



ምስል 5.11፡ የማህበረ-ሰብ አሰፋፈር

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- የሰው አካል የሙዚቃ መሣሪያ ነው፡፡ማለትም የሰውነት አካላችን በማወዛወዝ አስደናቂ የቡድን ሙዚቃን ለመፍጠር ጠቃሚ መሣሪያ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሙዝቀኛ የሚይዘውን የሙዚቃ መሣሪያ በሰውነት አካላችን በመያዛችን በማይታመን ሁኔታ ተደራሽ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ደረጃ ለሙዚቃ ትምህርት አስፈላጊ የሰውነት አካል ነው፡፡
- ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ እርስበርስ የተሳሰሩ እና ተምሳሌታዊ ናቸው፡፡
- የትወና እና የእይታ ጥበብ የቋንቋ ትምህርትን በቀላሉ ለማስተማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ይህም ማለት የአማርኛም ይሁን የእንግሊዝኛን ፊደላት በቀላሉ አሳምራችሁ እንድትጽፉ ፊደላትን እንዴት መቅረጽ እንዳለባችሁ ከስነ ጥበባት ትምህርት መካከል በስዕል ዘርፍ ትማራላችሁ፡፡

## ማጠቃለያ መልመጃ

1. ስለምትወዱት የትምህርት አይነት አንድ የሙዚቃ ግጥም ጻፉ፡ ፡ለምሳሌ ስለ ሂሳብ፣ አካባቢ ሳይንስ፣ እንግሊዘኛ ወይም አማረኛ የሚገለጽ መዝሙር ግጥም ጻፉ፡፡
2. የግብይት ስርአት የሚያሳይ ስዕል ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
3. ትወና ትምህርትን ለመማር ያላቸው አስተዋጽኦ የሚያሳይ ድራማ ሰርታችሁ ለክፍል አሳዩ፡፡

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ

1. ዜማ፣ስልተምት (ሪትም) ፣ሃርመኒ(ህብረ ዜማ)ያለቸዉ ድምፆች ሁሉ _______________ለማለት እንችላለን
   ሀ. ሙዚቃ  ለ. ስዕል  ሐ. ድራማ
2. የሙዚቃ አላባዊያን የሆነዉ የቱ ነዉ
   ሀ. ዜማ
   ለ. ሜሎዲ
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸዉ
3. የእይታ ጥበብ አላባዊያን እና መህር የሆነ የቱ ነዉ
   ሀ. መስመር
   ለ. ስልተ ምት
   ሐ. ሪትም
4. ልጆች ቤት ዉስጥ ያዩትን የእናት የአባትን ባህሪ እና ድርጊት በምን ያሳያሉ
   ሀ. በጨዋታ(በትወና)
   ለ. በመረመድ
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸዉ

# እንማር


እንማር እንማር
እንመራመር
ትምህርት ያስፈልጋል
በዕውቀት ለመኖር
ተፈጥሮን ህይወትን
ለመቃኘት በውል
ድራማ ሙዚቃ
ደግሞ ስነ-ስዕል
በሦስተኛ ክፍል
እስከምንገናኝ
ክረምቱ በጥናት
እናሳልፋለን